አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና የኮሚኒሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል


ድኅረ ምረቃ መርሀግብር

# ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ (በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ በጅማ ወለኔ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት


በ

የሰራሽ አደራው


ሐምሌ/2016

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያዊ

# ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችንት የመጻፍ ችሎታ እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ (በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ በጅማ ወለኔ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲ፣ ቋንቋዎችጥናት፣ጋዜጠኝነትናኮሞኒዩኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍ ፎክለር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

(በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር )

ለኤም ኤ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

የጥናቱ አማካሪ

ግርማ ገብሬ (ዶ/ር)

ሐምሌ/2016

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያዊ

# ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ (በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ በጅማ ወለኔ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤ በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናኑ ፣ ጋዜጠኝነትና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፋ ፎክለር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ

የሰራሽ አደራው

የፈተና ቦርድ አባላት

------------------------------ ----------------------------

አማካሪ ፊርማ

-------------------------------- --------------------------

ፈታኝ ፊርማ

---------------------------------- -------------------------------

# ምስጋና

የጅማሬና የፍጻሜ ባለቤት፤ ምስጋና የባህርይ ገንዘቡ ለሆነው አምላክ በሁሉም ነገሬ ስለደገፈኝና ስላበረታኝ ዘላለማዊ ምስጋናዬን ለእግዚአብሔር አቀርባለሁ፡፡

ጥናቱን ስጀምር ጀምሮ እስካጠናቅቅ ድረስ ከፍተኛ ትዕግስትና ብልሃት በተሞላበት አኳኋን ከዕውቀታቸውና ከጊዜያቸው ሳይሰስቱ ቅንነት በተሞላበት ጥናታዊ ጽሁፉን በማንበብ የተንጋደደውን በማረምና በማስተካከል ገንቢ አስተያየትና ጥቆማ በመስጠት እንዲሁም የተለያዩ መረጃዎችን በማፈላለግና በማሟላት ጥናቱ ፈር እንዲይዝ ከፍተኛውን ድርሻ ለተወጡት አማካሪዬ ለዶ/ር ግርማ ገብሬ  ጥልቅ የሆነ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ትምህርቴን ላስተማረኝና ጥናቱን  በማከናውንበት ግዜ ወጭዬን በመሸፈን ለተባበረኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቴ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመጠቆም እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ የሆነውን ድርሻ ለተወጣው ባለቤቴ ለመ/ር አበበ በቃሉ ስለመልካም ትብብሩ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የእኔን እዚህ ደረጃ መድረስ በከፍተኛ ደረጃ በጉጉት ለሚጠብቁት ቤተሰቦቼ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የትግበራ ስራውን በመስራት በሃሳብና በሞራል ሲደግፉኝና ሲያበረታቱኝ ለነበሩ የስራ ባልደረቦቼ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ለተግባሩ ተሳታፊ ለነበሩ ተማሪዎች በሙሉ ምስጋናዬ ከልብ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ


**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ vi

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ደራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.3 የጥናቱ አላማ ........ 5

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5

1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.6 የጥናቱ ውሱንነት ........ 7

1.7 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ብያኔ ........ 8

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳን ........ 9

2.1 ጽህፈትን እንዴት እናስተምራለን? ........ 9

2.2 የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ መንገዶች ........ 12

2.2.1. ውጤት - ተኮር አቀራረብ ........ 12

2.2.2. ሂደት -ተኮር አቀራረብ ........ 13

2.2..3. ዘውግ ተኮር ........ 17

2.3 የተነሳሽነት ምንነት ........ 18

2.4 የተነሳሽነት ዓይነቶች ........ 19

2.5 የተነሳሽነት መገለጫዎች ........ 20

2.5.1 ግለ ብቃት (Self Eficacy) ........ 20

2.5.2 ግለ መር (Self Regulation) ........................................................ 20
2.5.3 ግለ ግንዛቤ (Self Concept) ፡ ........................................................ 21
2.6 ተነሳሽነት ከመጻፍ ክሂል ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ........................................................ 21
2.7 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........................................................ 21
ምዕራፍ ሶስት
የአጠናን ዘዴ ........................................................ 24
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........................................................ 24
3.2 የናሙና አወሳሰድ ........................................................ 24
3.3 የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎች ........................................................ 24
3.3.1 ፈተና ........................................................ 25
3.3.2 የፅሁፍ መጠይቅ ........................................................ 25
3.4 የትግበራ ሂደት ........................................................ 25
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................................ 25
3.6 የጥናቱ ስነምግባራዊ ሁኔታ ........................................................ 26
ምዕራፍ አራት
የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........................................................ 27
4.1. የውጤት ትንተና ........................................................ 27
4.2 የውጤት ማብራርያ ........................................................ 35
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች ........................................................ 37
5.1. ማጠቃለያ ........................................................ 37
5.2. መደምደሚያ ........................................................ 40
5.3. የመፍትሔ ሀሳቦች ........................................................ 40
ዋቢ ፅሁፎች ........................................................ 42
አባሪዎች ........................................................ 46

# አባሪዎች

አባሪ ሀ, የቅድመ ትምህርት ድርሰት የመፃፍ ፈተና

አባሪ ለ, የድኅረ ትምህርት ድርሰት የመፃፍ ፈተና

አባሪ ሐ, በተማሪዎች የሚሞላ የተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ

አባሪ መ. የቅድመና ድህረ ሙከራ ፈተና ውጤት

አባሪ ሠ,የቅድመ እና ድኅረ የመጻፍ ክሂል ፈተናዎችን ለማረም ተግባር ላይ የዋለው ሞዴል

አባሪ ረ. በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና የድህረተነሳሽነትንለመፈተሽ የተሞላው የፅሁፍ መጠይቅ

አባሪ ሰ. በሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ተነሳሽነትን ለመፈተሽ የተሞላው የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት

**የሠንጠረዝ ማውጫ**

ሰንጠረ ዥ 1 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ የመጻፍ ፈተና ችሎታ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ- ቴስት ........ 27

ሰንጠረዥ 2 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ የመጻፍ ፈተና ችሎታ ንጽጽር.... 28

ሰንጠረዥ 3 የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ የመጻፍ ችሎታ ንጽጽር በዳግም ናሙና ቲ ቴስት ........ 29

ሰንጠረዥ 4 የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመና ድህረ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ንጽጽር በዳግም ናሙናቲ -ቴስት ........ 30

ሰንጠረዥ5 የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ተነሳሽነት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ንጽጽር በዳግም ናሙና ቲ-ቴስት ........ 31

ሰንጠረዥ 6 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የድህረ ተነሳሽነት ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት ........ 32

ሰንጠረዥ 7 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ተነሳሽነት ንፅፅር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ........ 33

ሰንጠረዥ 8 የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረተነሳሽነትንፅፅር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት 34

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናታዊ ጽሁፉ ዋነኛ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የሂደት ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችየመጻፍ ክሂል ችሎታ እና ተነሳሽነት ከማሻሻል አንጻር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱም ከፊል ሙከራዊ ሲሆን፣ የተካሄደውም በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ በሚገኘው በጅማ ወለኔ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል የ9ኛክፍል ተማሪዎች በአመቺ የናሙና ስልት ከተመረጡ በኋላ፣ በተራ ዕጣ የናሙና አመራረጥ ስልት በአንድ መምህር የሚማሩ ሁለት ምድብተማሪዎች ተለይተው በቅድመ ፈተናው ሂደት ተሳትፈዋል፡፡ ከሁለቱ ምድቦች መካከል በቅድመ የመጻፍ ክሂል ፈተና ተቀራራቢ አማካይ ውጤቶች ያስመዘገቡ ሁለት ምድቦች ከተለዩ በኋላ በተራ የዕጣ ናሙና ስልት አንዱ የሙከራ ሌላኛው የቁጥጥር ቡድን ሆኖ በጥናቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ተደርጓል፡፡ በመረጃ መስብሰቢያ ዘዴነት ፈተና እና የጽሑፍ መጠይቅ ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ፈተናው፣ ቅድመ እና ድኅረ ፈተናን ያካተተ ነው፡፡ ቅድመ ፈተናው የተሰጠበት ዓላማ ተማሪዎች ከሙከራ ጥናቱ በፊት ያላቸውን የመጻፍ ክሂል ውጤት ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ሲባል ነው፡፡ የድኅረ ፈተናው ዓላማ ደግሞ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ሆነው የተመረጡት ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ክሂልን ከተማሩ በኋላ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ነው፡፡ በሌላ በኩል የጽሑፍ መጠይቅ የተማሪዎቹን የመጻፍ ተነሳሽነት ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ተተኳሪ የሆኑት ተማሪዎች ከመጻፍ ልምምዱ በፊት (ቅድመ ጽሑፍ መጠይቅ) እና በኋላ (ድኅረ የጽሑፍ መጠይቅ) እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በቅድመ ፈተና እና በቅድመ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች በዳግም ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ እንዲሁም በድኅረ ፈተና እና በድኅረ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች በባዓድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ዘዴ እንዲሰሉ ተደርጓል፡፡ የተገኙት ውጤቶች እንደሚያመለክቱት በቅድመ ፈተና እና በቅድመ የጽሑፍ መጠይቅ ተመጣጣኝ አማካይ ውጤቶች የተመዘገበባቸው ቡድኖች፣ በድኅረ ፈተና ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣የቋንቋ አጠቃቀም እና ሥርዓተ አጻጻፍ እና በድኅረ የጽሑፍ መጠይቅ ተነሳሽነት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይተዋል፡፡ይህም ውጤት የሂደት ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ እና ተነሳሽነት ከማሻሻል አኳያ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ሊጠቁም ችሏል፡፡ ከመጻፍ ክሂልችሎታ እና ተነሳሽኘት አንጻር የተገኙት ውጤቶች ላይ በመመስረት ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ከተደረገ በኋላ፣ የሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር ጥሩ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ መምህራን ጥሩ ግንዛቤ ኖሯቸው በክፍል ውስጥ በተገቢው ሁኔታ መተግበር እንዲችሉ የሚያደርጋቸው በቂ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የመፍትሄ ሀሳቦች እና የጥናት ጥቆማዎች እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ደራ

በቋንቋ ተግባቦት ሂደት መሰረታዊ ከሚባሉት አራቱ ክሂሎች አንዱ መጻፍ ሲሆን ለሀሳብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል ነው።መጻፍ የተለያዩ ጽሁፋዊ ከንውኖች የመጨረሻ ውጤት የሆነ የሀሳብ ማስተላለፊያ ነው Tangerparmpoon(2009)በማለት ይገልፃሉ። የመፃፍ ክሂል ከንግግር ክሂል የመጣ ቢሆንም ለሰው  ልጆች የሚሰጠው ጥቅም ከፍ ያለ ሲሆን በዋናነት እውቀት የሚቀስምበትና የሚተላለፍበት፣ታሪክ የሚ መዘገብበት ከዘመን ወደ ዘመን የሚሸጋገርበት ድልድይ ሆኖ ያገለግላል (Tangerparmpoon, 2009)።

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣት ይጠይቃል። የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም እንዲሁም የዓረፍተ ነገር አወቃቀር እና የአንቀጽ አመሰራረት ለክሂሉ በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች፣ ስነዘዴዎችና አመለካከቶች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የየራሳቸው ስሌቶች አሏቸው። በመስኩ ምሁራን ተደጋግመው የሚጠቀሱና ተቀባይነት ያገኙ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር ከሚያገለግሉ አቀራረቦች መካከል በተጠናቀቀ ፅሁፍ ላይ የሚያተኩረው ውጤታዊ አቀራረብ፣ በፅሁፍ ሂደት ላይ ትኩረት የሚያደርገው እና መፃፍን ዓላማ ያለው እና ድርጊት የሚከናወንበትን አውዳዊ አገባብን በመተንተን ትኩረት የሚያደርገው የሂደት ተኮር አቀረቀረብ መሆናቸውን ይገልጻሉ (Brown, 2001 እና Atikinson, 2003)።
አማረ (2010)  እንደገለጹት የመጻፍ ክሂልን በትምህርትነት መስጠት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የተለያዩ አቀራረቦች አገልግሎት ላይ ውለዋል።  የመጀመሪያው የሆነው ውጤታዊ አቀራረብ እንደሆነና፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት በስፋት አገልግሎት ይሰጥ እንደነበር ገልጸዋል። የዚህ አቀራረብ ዓላማም ተማሪዎች የአጻጻፍ ስርዓቶች ትምህርት ላይ ተመስርተው የመጻፍ ክሂልን እንዲማሩ ማስቻል ነው። ውጤታቸው የሚረጋገጠው ተማሪዎች የሚጽፉትን የመጨረሻ ድርሰት በጥልቀት በማረም ነው። ይህ አቀራረብ ለቅርጽ ሰፊ ትኩረት መስጠቱ፣ ተማሪዎቹ በራሳቸው ልዩ ልዩ ተግባቦታዊ ተግባራትን እየፈጠሩ እንዲለማመዱ የማደረጉ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ፣ እንዲሁም የትምህርቱ ሂደት መምህር ተኮር በመሆኑ በደካማ ጎን የሚነሱበት ነጥቦች ናቸው ይላሉ። Burden, Larson and Toonen (2005) እንደገለፁት ቀደም ባለት ጊዜዎች

እስከ 1970 ዎቹድረስ መምህራን በመፃፍ ትምህርት ወቅት ትኩረት የሚያደርጉት በመጨረሻው ውጤት ላይነው:: ውጤታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚናዝቅተኛ እንደሆነ ከተረጋገጠ በኋላ ሂደታዊ አቀራረብ ሊመጣ ችሏል፡፡ ሂደታዊ አቀራረብም በመፃፍ ክሂል ማስተማሪያነት ማገልገል የጀመረው ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ መሆኑን እና ለውጤታዊ አቀራረብ በተቃውሞ የቀረበ አፀፋ ነው (Yan, 2005) ይላሉ፡፡

ሰይድ (1993) እና አለማየሁ( 1986): በእነዚህ ሁለት ተመራማሪዎች የቀረቡ ሥራዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ሲሆኑ፣ በማጠቃለያቸው ሰይድ (1993) ልማዳዊውን የማስተማር ስነ ዘዴ ለመለወጥ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ሲገልጹ፣ አለማየሁ (1986) በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ብዙ መሆን እና የክፍለ ጊዜው አነስተኛነት ተማሪዎች ድርሰት እንዲጽፉ እና እንዲለማመዱ ለማድረግ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ፅሁፍ አርመው በጊዜ ለመመለስ የሚጠቀሙበት ልማዳዊ የማስተማሪያ ዘዴ አመቺ እንዳልሆነ በመግለጽ በማስተማሪያ ዘዴው ላይ ጥናት እንዲካሄድ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::

በመሰረቱ  ፅህፈትን ለማስተማር የተለያዩ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ የፍላጎት፣ የችሎታና የዝንባሌ ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ የመምህሩ የአቀራረብ ዘዴና የማስተማሪያ መሳሪያዎችም እንደሁኔታው የሚያሳድሩት ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ የተማሪዎች እና የክፍለ ዜያት መብዛት በመምህሩም ላይ የሚያስከትለው ጫና የወቅቱ አብይ ችግር ነው፡፡አጥኝዋ በማስተማር ልምዷ ያስተዋለችው ጉዳይ እንደሆነ ለመግለጽ ትወዳለች ፡፡  የዚህ ጥናት አቅራቢም በምታስተምርበት  የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባስተማረችባቸው ጊዜያት በተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ላይ ችግሮችን በማስተዋሏ እና ይህም ከሚከሰትባቸው  ዋነኛው የማስተማሪያ አቀራረብ በመሆኑ በሂደት ተኮር አቀራረብ ላይ ፍተሻውን አተኩራለች፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በተማሪዎች የሚታየው የመጻፍ ችግር የቋንቋውን ፊደሎች በትክክለኛው ቅርፅ ካለመጻፍ ይጀምራል፡፡ ከዚህ ባለፈም ሰፋ ያሉ ሀሳቦችን በተገቢ አደረጃጀት አለመጻፍ፣ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን በጽሁፋቸው ውስጥ አለመጠቀም፣ ሰዋስዋዊ ስርዓታቸውን የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን

ማዋቀር አለመቻልና የመሳሰሉት ችግሮች በብዙ ተማሪዎች ዘንድ እለት በዕለት የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው (Baroch & kashavarie, 2002 & Eazrig, 2006)፡፡በተማሪዎች ላይ የሚፈጠሩ ችግሮች ከቋንቋ ችሎታ/ ውጤታማነት እና ግንዛቤ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህንን ሀሳብ ማረው (1996) እንደገለፁት በአማርኛ ቋንቋ አውድ ላይ ተመስርተው እንደሚገልጹት በመጻፍ ትምህርት ሂደት በተማሪዎች ላይ የሚከሰቱ ችግሮች እንዳሉ በመግለጽ፣ እነዚህንም ችግሮች በሶስት መልኩ ይመለከቷቸዋል፡፡ እነሱም፣ የሀሳብ እጥረት ወይም የሚጽፉት ማጣት፣ የቋንቋ ችሎታ ማነስ እና ሀሳብን በአግባቡ ማደራጀት አለመቻል ናቸው፡፡ Mohamed (2015) እንደሚገልጹት ተማሪዎች ከፊደል አጻጻፍ ሥርዓት፣ ከሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ከይዘት፣ ከቃላት፣ ከዓረፍተ ነገር አወቃቀር እና ከአደረጃጀት አኳያ ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል፡፡በሌላ በኩል በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ላይ ትኩረት ካደረጉ ጥናቶች መካከል ተመስገን (2001) እና ሀና (2003) ጥናቶች እንደጠቆሙት ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እንዲለማመዱ የማድረጉ ሁኔታ መምህር መራሽ አቀራረብ ላይ ማተኮሩ የተማሪዎችን የመጻፍ
ችሎታ ክፍተት ያለበት እንዲሆን መንስኤ ሊሆን ችሏል፡፡አማረ (2010) (Bandura, 1986) ጠቅሰው እንደገለጹት ከስነ ልቦናዊ ገጽታዎች ውስጥ አንዱ፣ ተነሳሽነት ነው፡፡ ተነሳሽነት በመጻፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ የተማሪዎች ተነሳሽነት በጨመረ ቁጥር፣ ችግሮችን የመፍታት አቅማቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ችግር የመፍታት አቅም ሲጨምር፣ ተማሪዎች የተሰጣቸውን የመጻፍ ተግባር በክፍል ውስጥ ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲተገብሩ ያስችላቸዋል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያስቡ ከሆነ ወይም ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ ከሆነ፣ ዝቅተኛ የመጻፍ ችሎታ እንዲኖራቸው ምክንያት ይሆናል፡፡ በዚህም የተነሳ በትምህርቱ ሂደት ብዙ ስህተቶችን ይፈጽማሉ፤ እንዲሁም ችሎታ የለኝም ብለው ስለሚያስቡ ውስብስብ ችግሮችን ለማለፍ አይደፍሩም፡፡በሌላ Alamirew (2005), Ebabu (2013) እና Mesfin (2013) እንደሚገልጹት በመጻፍ ትምህርት ሂደት ለሚፈጠሩ ችግሮች እንደምክንያት ከሚነሱ መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሰው የማስተማሪያ ዘዴ ተጽዕኖ ነው፡፡ ለመጻፍ ትምህርት ተግባር ላይ የሚውለው የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎቹ በበቂ ሁኔታ እንዲለማመዱ የማያስችል እና ተግባቦት ላይ ያልተመሰረተ ከሆነ ለችግሩ መፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ላይ ትኩረት ካደረጉ ጥናቶች መካከል ተመስገን (2001) እና ሃና (2003) ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በተግባር እንዲለማመዱ የማድረጉ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ እና የትምህርቱ

ሂደት መምህር መራሽ አቀራረብ ላይ ማተኮሩ፣ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ እና ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንዲሆን መንስኤ ሊሆን ችሏል፡፡ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ሂደት ለሚፈጠሩ ችግሮች በተለያዩ አጥኚዎች የተነሱ ምክንያቶች ከአጥኝዋ የግል ገጠመኝ ጋር ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡ ይኸውም፣ አጥኚዋ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በምታስተምርበት ወቅት ተማሪዎች የሚጽፏቸው ድርሰቶች ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቃላት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ እና ከሥርዓተ አጻጻፍ አንጻር ችግሮች እንደሚታይባቸው እንዲሁም ለመጻፍ ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑን ታስተውል ነበር፡፡

ከዚህም ሂደት በኋላ አጥኝዋ ከመጻፍ ክሂል ጋር በተያያዙ ልዩ ልዩ ጥናቶች ውስጥ በመሳተፍ እና ተጨማሪ ንባቦችንም በማድረግ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት አለመሻሻል የሚነሱ ነጥቦችን እንድትለይ አስችሏታል፡፡ አጥኝዋም፣ ካነበባቻቸው ጥናቶች መገንዘብ የቻለችው መምህራን የሚከተለውን የማስተማሪያ ዘዴ ለተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት አለመሻሻል ምክንያት እንደሆነ ነው፡፡የዚህ ጥናት አቅራቢም በገደባኖ ወረዳ በተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ባስተማረችባቸው ዓመታት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን እና ችግሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ መሄዱን ማጤን ችላለች:: የችግሩን መንስኤ በመፈተሸ የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን በማመን በመፃፍ ክሂል ትምህርት ዙሪያ የተካሄደ ቀደምት ጥናቶች በትምህርቱ አቀራረብ ላይ ድክመት መኖሩን አመላክተዋል:: በዚህም ምክንያት ቀደም ሲል የተማሪዎችን ሀሳብን በጽሐፍ የመግለጽ ችሎታ ለማዳበር ያስችላል የተባለው የሂደት ተኮር አቀራረብ የአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ማስቻል አለማስቻሉን ማረጋገጥ የሚለው ለጥናቱ እንደ አነሳሽ ምክንያት ታይቷል::

የዚህ ጥናት ዋነኛ አነሳሽ ምክንያት የሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል የሚያሻሻል መሆን አለመሆኑን የመፈተሽ አላማ ያለው ሆኖ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ጥረት ይደረጋል፡፡

- ተማሪዎች በሂደት ተኮር ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደረጉ በኋላ ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸው ይሻሻላል?
- በሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች ከልምምድ በኋላ ተነሳሽነት ላይየመፃፍ መሻሻል ያሳይ ይሆን?

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ ሂደት ተኮር አቀራረብ  የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ  እና ተነሳሽነት መፈተሽ ነው። ይህ አብይ አላማ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት።

- የድርሰት አጻጻፍ ክሂልን ትምህርት ለማጠናከር ።
- ተማሪዎች  በሂደታዊ ዘዴ የሚቀርብላቸውን ትምህርትና ልምምድ ይወዱታል ? ለምን ?
- በሂደታዊ የድርሰት አጻጻፍ ትምህርት ወቅት የሚከሰቱ ችግሮችን ለማቃለል።
- ከተማሪው ብዛት የተነሳ መምህሩ ድርሰትን አርሞ ለመመለስ ያለበትን ጫና የሂደታዊ ድርሰት መጻፊያ ዘዴ ሊያረግበው ይችላል ?የክፍልና የቤት ስራን በማቀናጀት ፣የቡድን ስራንና የብጤ አርማትን ስልት በማስተዋወቅ ና በማለማመድ መልሶ ምግባር በመስጠት ድርሰትን ለመጻፍም ሆነ ለማረም አጋዥ የሆነ የማመሳከሪያ ዝርዝርም ማቅረብና አጠቃቀሙን ለማስረዳት ።
- ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ክሂል ለማሻሻል ያለውን ፋይዳ መፈተሽ፣
- በዚህ ዘዴ ከማስተማር  ጋር ምን ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ? ከሚገኘው ውጤት በመነሳት የሂደታዊ ዘዴ ከነባራዊ ችግር አካያ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሚኖረው ለማየት ይሞክራል።
- ሂደት ተኮር አቀራረብ በተ ማሪ ዎች የመፃፍ ክሂል ትምህርት ላይ ተነሳሽነት አኳያ ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህጥናት የተመሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ማጎልበት የሚቻልበትን አቀራረብ የሚያጠና በመሆኑ የሚከተሉት ተግባራዊ እና ስነ ትምህርታዊ ፋይዳዎች ይኖሩ ታል ተብሎ ይታሰባል።

- ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ከማዳበር አኳያ ሂደት ተኮር አቀራረብ የሚኖረው ተጽዕኖ ምን እንደሆኑና የተጽዕኖው ደረጃም ምን ያህል እንደሆነ ተረድተው በተግባሩ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ግንዛቤ ያስጨብጣል፤
- ድርሰት ለመፃፍ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎችን  ክሂል ለማሳደግ የሚያግዝ አማራጭ ለመፈለግ፡፡
- የፅህፈት መምህራን በተማሪዎች ፅሁፋዊ ስራዎች ላይ ተገቢ አቀራረቦችን በመፈተሽ እና እዲጠቀሙ ወይም ሌሎች የአቀራረብ ምንጮችን በአማራጭነት መፈተሽ እንደሚኖርባቸው ሊያመለክት፣
- የመማር የማስተማሪያ መጽሐፍ ወይም የመርሃ ትምህርት እና ስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ከሂደት ተኮር አቀራርብ ጋር በተገናኘ በመፃፍ ክሂል ትምህርት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት እንዲያስችል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በገ/ጉ/ወ/ወ በጅማ ወለኔ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለዉን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ጥናት ለማክናወን  አጥኝዋ የተጠኝዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታ ለመፈተሽ በጅማ ወለኔ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ በ2015 ዓ/ም  የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አራት ክፍል ሲሆኑ ከዚህ ዉስጥ ሁለት ክፍል ተመሪዎች በተራ የዕጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ በሂደት ተኮር አቀራርብ ለሚለማመዱ ተጠኝዎች የድርሰት ትምህርት ተሰጧቸዋል፡፡ስለድርሰት ሂደት ከአጥኝዋ ማብራሪያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

ከዚህ ባለፈ ከዝርዝር  የድርሰት አፃፃፍ ዘዴዎችና ውጤታማነታቸው ነፃ የሆነው ተላውጦዎች ሂደት ተኮር አቀራረብ ከጥገኛ ተላውጦ ድርሰት የመፃፍ ችሎታና ተነሳሽነት ማሳደግ ጋር ያለውን ንጽጽር ብቻ ይመለከታል፡፡ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን በክፍል ደረጃና በጾታ ልዩነት ያለውን ተግባር አይመለከትም፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ለውጥ ማሳየቱን ወይም አለማሳየቱን የሚያመለክተዉ ከተማሪዎች ፁሁፋዊ ስራዎች ይዘት የሀሳብ አደረጃጀት፣ ቃላት አመራርጥና አጠቃቀም፣የቋንቋ አጠቃቀም፣ እንዲሁም ስርዓተ ፅህፈት አንፃር ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውሱንነት

በዚህ ጥናት ውስጥ ከአጥኟዋ እና ከተማሪዎች እንዲሁም ከቀደምት ጥናቶች አንጻር የሚነሱ ውሱንነቶች አሉ፡፡በዚህ ጥናት ውስጥ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በአንድ መምህርት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ከዚህ አኳያ መምህርቷ በሂደት ተኮር የመፃፉ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ፣ የቁጥጥር ቡድኑን በተለምዷዊው የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ስታስተምር  በመጀመሪያዎቹ የአተገባበር ሂደቶች በሁለቱም ቡድኖች ላይ ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት አቀራረብ ያልተሰጠበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይህንንም ሁነት ማረጋገጥ የተቻለው በክፍል ውስጥ የአተገባበር ሂደት ነው፡፡ ችግሩንም ለመቅረፍ ለቁጥጥር ቡድኑ የማካካሻ ትምህርት ሰዓት በማመቻቼት በሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማሪያ ዘዴ ተሰጥቷል ፡፡

በሁለተኛ ደረጃነት የሚጠቀሰው ከተማሪዎች አንጻር የታየ ውሱንነት ነው፡፡ በተሰጠው የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ  በተለይም ተማሪዎች በመጀመሪያዎቹ ክፍለ ጊዜያት የሚያከናውኗቸው የመጻፍ ተግባራት ላይ የመደናገር ስሜት ይነበብባቸው ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት የማስተማሪያ ዘዴው አዲስ መሆን እንደሆነ አጥኟዋ ለመረዳት ችላለች፡፡

ከዚህ አንጻር የታዩ ችግሮችን ለመፍታት ተመራማሪዋ የተማሪዎችን የመደናገር ስሜትን ለመቀነስ ከተቻለም ለማጥፋት መከናወን የሚገባቸው ዝርዝር የመጻፍ ክሂል ተግባራትን ለተማሪዎቹ በግልጽ ማሳየት እንደሚኖርባቸው በተመራማሪዋ በኩል የምክር ሀሳብ በመስጠት ውስንነቶቹን ለመቀነስ ጥረት ተደርጓል፡፡ በሌላ መልኩ በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ የሆኑት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ስለተማሩበት ዘዴ እና ስለአከናወኗቸው ዝርዝር ተግባራት ከክፍል ውጪ የሚያደርጓቸው ውይይቶች የራሳቸው የሆነ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም ከተማሪዎች አንጻር የተነሱት ውሱንነቶች በዚህ የጥናት ውጤት ላይ ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል፡፡በመጨረሻ ይህ ጥናት በዋነኝነት የሚመልሳቸው ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነሱም የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነትን መፈተሽ ነው፡፡ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለመፈተሽ አምስት አላባውያን (ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ሥርዓተአጻጻፍ) በጥናቱ ውስጥ በዝርዝር አላማነት ተካተዋል፡፡ ከዚህ የሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማር ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ በሌሎች ቀደምት ጥናቶች ሲፈተሽ ጥቅል የመጻፍ ክሂል ውጤትን እንጂ፣ በእያንዳንዱ የመጻፍ

ክሂል አላባውያን ላይ ጉልህ ልዩነት መኖር- አለመኖሩን የፈተሹ ጥናቶች አልተገኙም፡፡ ምንም እንኳን ከቃላት እና ከቋንቋ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ጥቂት ጥናቶች መገኘት ቢችሉም፡፡ ይህንንም ችግር ለመቀነስ የቀደምት ጥናቶቹ ከአጠቃላይ የመጻፍ ክሂል አንጻር ያገኟቸውን ግኝቶች በዚህ ጥናት ውስጥ በእያንዳንዱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን ላይ በማስተሳሰር ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡ከላይ ከቀረበው ጋር በተያያዘ ይህ ጥናት ከሚመልሰው መሰረታዊ ጥያቄ ውስጥ አንዱየተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ተነሳሽነትን መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማር ዘዴ ላይ ተመስርተው ከመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ጋር የተያያዙ ጥናቶች በበቂ ሁኔታ አለመገኘታቸው እንደውሱንነት ሊነሳ የሚችል ነው፡፡ ይህንንም ችግር ለመቀነስ በሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማር ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ላይ የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች ተገኝተው፣ በዚህ ጥናት ውስጥ የተነሳሽነት ገጽታዎች (ግለ ግንዛቤ፣ ግለ ብቃት እናግለ መር) ሆነው የቀረቡት ላይ በማጠናከሪያ ሀሳብነት እንዲያገለግሉ ተደርገዋል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ብያኔ

ተነሳሽነት፡-ንቁ በሆነ አዕምሮ (በሙሉ ንቃተ ህሊና)አንድንድርጊት ለመፈጸም የሚካሄድ ጥረትን የሚያበረታታ አዕምሮታዊ እና ስሜታዊ ቅስቀሳነው፡፡

ሂደት ተኮር አቀራረብ፡- አይነተኛ መገለጫው ፀሀፊው በመፃፍ ሂደት የሚፈጽማቸውን ተግባራት በመግለጽ ላይ ማተኮር ነው፡፡ ሒደት-ተኮር መጻፍ ማስተማሪያ አቀራረብ በውስጡ ስድስት ዓበይት የተለያዩ ሒደታዊ ተግባራትን ማለትም ማሰብ፣ ማቀድ፣ ማርቀቅ፣ መከለስ፣እንደገና መጻፍ እና ማሳተምን ያካትታል፡፡

የመጻፍ ችሎታ፡- ከመጻፍ አኳያ የይዘት፣የቃላት አጠቃቀም፣ የቋንቋአጠቃቀምና የሥርዓተ አጻጻፍ ድምር ውጤት ነው፡፡

ድርስት፡-የተለያዩ አካላትን በማገጣጠም ወይም በማዛነቅ አንድ ወጥ አካልን ለመመሥረት የሚደረግ የቃላት ፣የአንቀጾች ፣ስንኞች ወይም የአቅርቦት ሀሳብ ክፍሎች ቅንጅት ወይም ጽህፈትን ማለማመድ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 ጽህፈትን እንዴት እናስተምራለን?

Celcica murcica(1991) በሰፊዉ እንዳተተ ከመምህራን ስልጠና ጀምሮ የድርሰትን ትምህርት ሊታሰብበት እንደሚገባ ነው፡፡እርሳቸው እንደሚሉት መምህራን በሚሰለጥኑበት ግዜ ትኩረት ሊደረግለት የሚገባው የጽህፈት ክሂልን ለመለማመድ ስርዓተ ትምህርትን ለመንደፍና ክፍልን ለመቅረጽ እንዲችሉ ከፍተኛ ግምት መስጠትና ጥንቃቄ መድረግነው፡፡Murray (1982) ድርሰትን እንዴት ማስተማር አንደሚገባ የራሳቸውን አስተያየት እንደሚከተለው ይሰጡናል፡፡ እንደርሳቸው አመለካከት የድርሰትን ትምህርት ከውጤት አኳያ ሳይሆን ከሂደት አኳያ ማስተማር ይጠቅማል፡፡መሰረታዊ የሆነውን የአጻጻፍ ሂደት ሰናስተምራቸው በጽሑፍው ውጤት ላይ ብቻ በማተኮር ተማሪዎችን ሰናስተምራቸው ትምህርቱን እንዲጥሉት እናደርጋቸዋለን እነርሱንም በደካማነታቸው ስለምንኮንናቸው ስሜቱም እንዳይኖራቸው ጥሩ ጽሁፍም እንዳይጽፉ እንቅፋፉ እንሆንባቸዋለን ስለዚህ ተጽፎ ያለቀለትን ጽሁፍ ይዘን ከምናስተምራቸው ይልቅ በመጻፍ ሂደት ባለ ጽሁፍ ተማሪዎችን ልናስተምር ይገባል፡፡በዚህ መንገድ ተማሪውን በተግባር ለይ የሚውለውን ቋንቋ እንጠቀማለን ለተማሪዎቻችን የቃላት አመራረጥና የቋንቋ አጠቃቀምን እናጋራቸዋለን፡፡ይህንኑ ሀሳብ Burack(1965) ይደግፉታል፡፡ተማሪው የሚጽፈው የአጻጻፉ ህግ የያዘ የመምሪያ መጽሐፍ ይዞ ሳይሆን የህይወት ገጠመኝን መሰረት አድር ቃላትን በመምረጥና ቋንቋውን በመጠቀም ነው፡፡ተማሪው ቋንቋን ተጠቅሞ ሀቅ ለራሱ እንዲገለጽለት በማድረግ የተገጸለትን ለሌሎች ለማስተላለፍ ይጥራል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ይንቃቃል፣ይበረታታል፣ከጥረቱ እየተማረ በውጤቱ ይደሰታል ፡፡

ለተማሪው የሚያስፈልገው ስለ አጻጻፍ ሂደት መጠነኛ ግንዛቤ ማስጨበጥና በሂደት የአጻጻፍ ክሂሉን እንዲያዳብር መረዳት ነው፡፡

በክፍል ውስጥ ልምምዱን በተመለከተ Don Byrne(1990)የሚሰጡትን አሰተያየት በድርሰት ትምህርት ተማሪዎች የድርሰትን ስራ በግል፣በጥንድ ወይም በቡድን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡አንዳንድ ክንውኖች በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ቢሆንም ተማሪዎች ስራውን በግል መጨረስ ይጠበቅባቸዋል ፡፡በመጀመሪያዎች የጽህፈት ደረጃዎች በህብረት እንዲሰሩ መደረጉ

ተገቢ ሲሆን ከሚሰጣቸው መልሶ ምገባ በኋላ ግን ለብቻቸው አስተካክለው እንዲጽፉ ቢደረግም ለክሂል እድገታቸው ጥሩ ይሆናል።
Celcia muricia (1991) ባጠናከሩት መጽሀፍ ውስጥ የተማሪዎች ልምምድ በክፍል ውስጥ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በቤት ስራም በኩል ሊሰጣቸው ይችል ይላሉሉ።ይችላሉ ።እርሳቸው እርሳቸው እንደሚሉት መምህሄ አንደሚሉት መምህሩ እንሚተልመው የትምህርት ግብ የቤት ስራውን ለተማሪዎቹ ይሰጣል።
ከአደረጃጀት ፣ከቅርጽ፣ከይዘን፣ከምክንያትና ውጤት ከንጽጽር ፣ከቅድመ ተከተል ወ.ዘ.ተ አኳያ የቤት ስራውን ለተማሪዎቹ ሊያዘጋጅ ይችላል ።እንደተፈለገው የትምህርት ግብ ተማሪዎች የራሳቸውን ርዕስ ሊመርጡ ወይም መምህሩ መርጦ ሊሰጣቸው ይችላል ።
እንደሌሎቹ ባለሙያዎች ፍልስፍና ደግሞ ድርሰትን ማስተማር ተማሪዎች የተገለጠላቸውን ና የደረሱበትን ነገር ማስተላለፍ የሚችሉበት መሳሪያ እንደሆነ አድርገው እንዲመለከቱት እንደሚረዳቸው ይገልፃሉ ።የሚሰጣውም የቤት ስራ ግላዊ ገጠመኞቻቸውንና መረዳታቸውን መተንተንና ማንጸባረቅ እንዲችሉ የሚረዳቸው መሆን ይገባዋል ይላሉ ።የዚህ አይነት አመለካከት ያላቸው ባለሙያዎች እንደሚሉት ከግል ገጠመኙ ተነስቶ ክሂሉን ያዳበረ ተማሪ የተለያዩ አካዳሚያዊ ጽሁፎችን ለመጻፍ የሚያስችለው ይሆናል ።በሌላ አባባል የክሂል ሽግግር ሊደረግ ይችላል ። የክፍልም ይሁን የበቤት ስራዎች ከተሰጡ በኋላ አብዛኛውን ግዜ ተማሪዎች የሰሩት ሰራ ሁሉ በመምህራቸው እንዲታረምላቸው ይፈልጋሉ።ነገር ግን እያንዳንዱን ነገር መመርመርና ማረም እንማያስፈልግ Don Byren (1990) ያስገነዝባሉ ።እንደ Byrne አመለካከት ተማሪዎች ያጠናቀቁትን የድርሰት ስራ በመቀያየር በጥንድ ወይም በቡድን እንዲያርሙ ቢደረግ መልካም ነው።ይህን በሚያደርጉበት ግዜ ጽሁፉን በሂሳዊ መንገድ የማንብ ልምድ ከማዳበራቸውም በላይ የራሳቸውን ስራ በዚሁ መልክ የማረም ልምድ ያዳብራሉ ።
የድርሰት እርማትን በተመለከተ Celcia Murcia (1991) የተጠናቀረ መጽሐፍ ውስጥ መምህሩ በዝርዝር ስህተቶች እርማት ላይ የሚያተኩር ከሆነ የድርሰት ትምህርት ማስተማሩ ቀርቶ የሰዋሰው ትምህርት ማስተማር ይሆንበታል የአጻጻፍ ደረጃው የተለያዩ ስህተቶች ቢፈጠሩም የተማሪን ስህተት ማረሙ ትኩረት ሊደረግለት የሚገባው በመጨረሻ በሚያቀርበው ስራው ላይ ቢሆን ይመረጣል ።
Kroll Chenoweth(1991) ጠቅሰው እንደማሉት በየደረጃው የተማሪውን ስህተት መጎርጎር ተስፋ ሊያስቆርጠው ይችላል ።ነገር ግን በማርቀቅ ፣በመከለስና በማቃናት ወቅት ሱናራስ

ኀደኛቹ ከድርሰቱ አላማ ፣ከተደራሲ፣ ከይዘት ፣ከአደረጃጀት፣ከቋንቋ አጠቃቀም ፣ከሥርዓተ ነጥብ አገባብ ወዘተ አኳያ ብዙውን ስህተት ማረም ይችላሉ ::Krol(1991) ድርሰትን እንዴት ማረም እንደሚገባ ራሱ ውስብስብ ስራ ነው ይላሉ::ነገር ግን መምህራን ከሚከተሉትመንገዶች መምረጥ እንደሚችሉ ያስረዳሉ ::

1,በህዳግ ላይ ለየት ያለ ምልክት (ቀስት) በማድረግ የስህተቱን አይነት መጠቆም ::

2,በስህተቱ ምትክ ትክክለኛ የሆነውን ጽፎ ማሳየት ::

3,ስህተት ብቻ መኖሩን ማመልከት ፤ለምሳሌ የቃል አመራረጥ የአረፍተ ነገር አወቃቀር የአንቀጽ ቅደም ተከተል ወ.ዘ.ተ

4,ዝርዝር ስህተቶች ላይ አለማተኮር ::

መምህሩ ከነዚህ መንገዶች ሁለቱን ወይም ከዚያ በላይ እንደ አላማው መጠቀም ፣አርሞ መልሶ ምግባር ማድረግ ቢችልም ጥናቶቹ እንደሚያመለክቱት በተማሪው ሊያስከትል ስለሚችለው ለውጥ በርግጠኝነት መናገር እንደሚቻል ነው ::ይህም ማለት በአንድ ዘገን እንደ መምህሩ የማረም ጥረት በተማሪው በኩል ተመጣጣኝ መሻሻል አልታየም የሚል የጥናት ውጤት ሲኖር ፤በሌላ ጥናት ደግሞ ተማሪዎች በሰዋሰው ላይ በተደረገላቸው መልሶ ምገባ በሚከልሱበት ወቅት አብዛኞቹ ለወጥ ያሳዪ ሲሆን ጥቂቶቹ መሻሻል አላሳዩም የሚል ውጤት አለ::

በአጠቃላይ የመልሶ ምግባ አላማው ተማሪው በጽሑፍ ከሂሉ መሻሻል እንዲያገኝ መሆኑን Kroll(1991) ያስመዘግባሉ ::እንደርሳቸው አባባል በተማሪው ድርሰት ላይ የመምህሩ መልሶ ምገባ ተጽኖ የሚያሳየው በጣም ዝቅተኛ ነው ስለዚህ የድርሰት መምህር የተለያየ የመልሶ ምግባር ስልት መቀየስና ተማሪዎችን ማሰልጠን ይጠበቅበታል ይላሉ::ተማሪው በየትኛውም መንገድ የሚሰጠዎ መልሶ ምገባ ወደፊት ለሚጽፈው ድርሰት አጋዥ እንዲሆንለት እንደሚጠበቅ አክለው ገልፀዋል ::መልሶ ምገባ በቃልና በጽሑፍ ሊሰጥ እንደሚችል Kroll(1991) ያመለክታሉ በተለይ ተማሪዎች ብዙ በሆነበት ክፍል ለያንዳንዱ ተማሪ መልሶ ምግባር ማድረግ የማይቻል ነው::በዚህ አይነት ክፍል ውስጥ በህብረት መስራት በብጤ እርማት ስልት ተጠቅሞ መልሶ ምገባ መስጠት ጠቃሚነት አለው::ተማሪዎችንም ለዚሁ ለዚሁ ተግባር ማዘጋጀት ይጠበቃል ::የማመሳከሪያ ዝርዝር ማዘጋጀት ናአጠቃቀሙን ማሳወቅ፣ማለማመድ ለታቀደው አላማ ግብ መምታት እንደሚበጅ Kroll(1991) ያሳስባሉ ::

Kroll(1991) እውነተኛ ድርሰትን የማስተማር ግብ ብለው የሚቆጥሩት ተማሪውን ቀስ በቀስ በማለማመድ ከመምህሩ ርቆ በሚሄድበት ግዜ ሀሳቡን በጽሁፍ በስርዓት መግለጽ እንዲችል የሚያስፈልገውን አጻጻፍ ስትራቴጅና መሳሪያዎችን ማስታጠቅ ነው።እንግዲህ ይህንኑ መሳሪያ ለማስታጠቅ የሚቻልበትን መንገድ በመሻት የሂደታዊ ዘዴን በማስተማሪያነት መመረጡን አጥኝዋ ገልጻለች።

## 2.2 የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ መንገዶች

የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ጉልህ ፋይዳ ያለው አይቀሬ ጉዳይ ከሆነ፣መጻፍን እንዴት እናስተምር? የሚለው ይሆናል።በርግጥ በአጠቃላይ ቋንቋን የማስተማሪያ ምርጥ ዘዴ ይህ ነው ማለት አስቸጋሪ መሆኑንየተለያዩ የቋንቋ ምሁራን (Celci mursha, 1991) ቢጠቁሙም፣ በየዘመኑ በብዙኀኑ ምሁራንዘንድ ተቀባይነት ካገኙት የየዘመኑ ፍልስፍናዎችና ከምናስተምራቸው ተማሪዎች ማንነት(አጠቃላይ ዳራ) አኳያ ተመራጭ ሊባሉ የሚችሉ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ምሁራን (Rechards, 1990፣ Bayran, 1991, Nunan, 1989) ቀርበው እናገኛለን:

በአጠቃላይም መጻፍ የማስተማሪያ ዘዴዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት ቢያዳግትም ከጥናቱ ርዕስ አኳያ ተዛማጅነት ያላቸውን፣ በአንጻራዊነትም ሲቃኙ የቅርብ ጊዜያት አቀራረቦች ሊባሉ የሚችሉና በተለያዩ ምሁራን (Lim, 2007, Feris, 2003, Badger & White, 2000) በተደጋጋሚ የተጠቀሱትን ሶስት አቀራረቦች፣ ማለትም ውጤት-ተኮር መጻፍንማስተማሪያ አቀራረብ፣ ሂደት- ተኮር መጻፍን ማስተማሪያ አቀራረብ፣ ዘውግ አቀራረብ ፣ምንነትና የአተገባበር ሂደታቸውን እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸውንና ያሉባቸውን እጥረቶች በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ አስተያየቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 2.2.1. ውጤት - ተኮር አቀራረብ

በJonson (1986) ገለፃ መሰረትም ውጤት-ተኮር አቀራረብ የበለጠ ጠቀሜታ የሚኖረው በጽሁፍ የመጀመሪያ እርከን እና በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ነውተብሎ ቢታመንም፣ ይህ ስነትምህርታዊ አቀራረብ ሌሎች ጸሀፍያንም ሀሳቦቻቸውን ውጤታማበሆነ ስልት እንዲያደራጁ ሊረዳቸው እንደሚችል ጠቁመዋል።በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ላይ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ የመጻፍ ክሂል ከማጎልበት አኳያ የተወሰኑ እጥረቶች ነበሩበት:: ውጤት-ተኮር አቀራረብ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚኖረው ጠቀሜታ፣ተማሪዎቹ ከቀረበላቸው ሞዴል ጽሁፋዊ ስራ ላይ፡- የሀይለቃልን፣ የመሸጋገሪያ ቃላትናሀረጋትን፣ የአንቀጽ

አገነባብ ስልትን፣ የሀሳብ አሰዳደር ስርዓትንና በአጠቃላይም የአጻጻፍ ብልሃት አተገባበር ስልትን እንዲረዱ የሚስችል መሆኑ ነው::

ውጤት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ሦስት የተለያዩ ደረጃዎች አሉት። እነዚህም፡- ውሱን-ፅህፈት (controlled writing)፣ መር- ፅህፈት (Guided writing) እና ነፃ ፅህፈት (Free writing) መሆናቸውን Richards (1990:107) ጠቁመው ምንነታቸውንና የአተገባበርሂደታቸውን በተመለከተም በስፋት አብራርተዋል::

ውጤት-ተኮር መጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና ለጀማሪ ጸሀፍያን ሞዴል ጽሁፋዊ ስራዎችን በማቅረብ፣ ሀሳባቸውን እንዴት አደራጅተው እንደሚያቀርቡ በመነሻነት ቢያገለግላቸውም፣ በሌላ በኩል ግን ችግሮች ያሉበት መሆኑን እንረዳለን:: ውጤት ተኮር አቀራረብ ላይ ከሚነሱት ሂሳዊ አስተያየቶች መካከልአንዱ ይህ አቀራረብ አንድ ወጥ የስህተት እርማት ስልትን ይከተላል የሚል ነው። ይህም ሂደት የተማሪዎቹን በራስ የመተማመንና የተነሳሽነት ስሜት ይቀንሳል ተብሎም ይታመናል።ውጤት-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎቹ ጥሩ ጸሀፊዎች እንዲሆኑ በማድረግ ለገሀዳዊው አለም በብቃት አያዘጋጃቸውም የሚለው ሌላው የመቃወሚያ ሀሳብ ነው። ከእነዚህም መካከል ውጤት-ተኮር አቀራረብ አንድን ጽሁፍ ለማዘጋጀት በተማሪዎች ወይም በጸሀፍያን ተግባራዊ መሆን ለሚኖርባቸው ነባራዊ ቅደም ተከተላዊ ተግባራት ትኩረት አአይሰጥም:: በውጤት-ተኮር አቀራረብ መምህራን ትኩረት የሚያደርጉት የተማሪዎች የመጨረሻው ረቂቃዊ ጽሁፍ፡- ከቃላት፣ከሰዋስው፣ ከሆሄያት እና ከስርአተ ነጥቦች አጠቃቀምና ትክክለኛነት አኳያ እንዲሁም ከይዘትእና ከአደረጃጀት አንጻር መገምገም ነው (Brown, 1994)።

በሌላ በኩል ከላይ በተጠቆሙት እና መሰል ሂሳዊ አስተያየቶች ምክንያት ምሁራን እነዚህን መሰል ችግሮች ሊቀርፍ ይችላልብለው ያሰቡትን ተከታዩን የመጻፍ ማስተማሪያ አቀራረብ (ሂደት-ተኮር አቀራረብን) በአማራጭነት አቅርበዋል::

### 2.2.2. ሂደት -ተኮር አቀራረብ

ተማሪው በሂደት የተለያዩ ደረጃዎችን እያለፈ እንዲመጣ ሳይሆን የታሰበው ግብ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግአቀራረብ ነው። በመሆኑም የጥሩ ፀሃፊዎች ሂደታዊ አቀራረብ ምርጫቸው አድርገዋል ።ሂደታዊ አቀራረብ አይነተኛ መገለጫው ፀሃፊው በመፃፍ ሂደት የሚፈጽማቸውን ተግባራት በመግለጽ ላይ ማተኮር ነው። በዚህ አቀራረብ በትክክለኛነቱ ምትክ የፀሃፊው የአፃፃፍ ሂደትከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል። የዚህ ፈለግ አራማጆች ትኩረት የሚያደርጉት በመጨረሻ

ተጠናቆ በሚቀርበው የጽህፈት ውጤት ሳይሆን ወደ እዚያ ለመድረስ የሚያስችለው ሂደት ላይ ነው፡፡ፀሃፊውም አዘውትሮ እራሱን የሚጠይቀው ስለጽሐፉ አላማና ስለአንባቢያን ሳይሆን ጽሁፉን እንዴት ሊጀምረው እንዴትስ ሀሳቤን አቀናጅቼ ልፃፈው የሚል ጉዳይ ላይ ነው በማለት Raymis (1983) ያስረዳሉ፡፡ በዚህ የመጻፍ አቀራረብ ተማሪዎች ድርሰታቸውን የሚጽፉት በውጤታዊ አቀራረብ እንደሚዘወተረው በመምህሩ ተወስኖ በሚሰጣቸው ርዕስ አይደለምም፡፡እራሳቸው የሚሰማቸውን ርዕስ ይመርጣሉ፡፡ የጽሁፋቸውን ረቂቅ ለመምህራን ለጓደኞቻቸው ያሳያሉ፡፡ የሚያገኙትም ምላሽ ይበልጥ እንዲያስቡበት ይገፋፋቸዋል፡፡

በመጻፍ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎች አሉ፡፡ የመጻፍ ስራ የሚያከናውነው ሰውሊያከናውናቸው የሚገቡ ነገሮች ለመፃፍ መነሳት ሀሳቦችን ማገናኘት፣ ሀሳብን በቢጋር መልክማዘጋጀት፣ ማስታወሻ መውሰድና የመጀመሪያውን ረቂቅ መፃፍ መከለስ፣ እንደገና ማቀድ፣ደግሞ ማርቀቅ በመጨረሻም ለህትመት ማዘጋጀት በተባሉት ክዋኔዎች ውስጥ እንደሚያልፉ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች ቅድመ ጽህፈት፣ የጽህፈት ጊዜ እና ድህረ ጽህፈት በሚባሉ ዋና ዋና የጽህፈት እርከኖች እንደሚከፈሉ Richards (1990) እና Hedge (1988) ያብራራሉ፡፡መምህራንም ተማሪዎች ሃሳብ ማፍለቅ እንዲችሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያነቃቃሉ፡፡ እየተመሩ መፃፍ በአብዛኛው ተማሪ ተኮር ሲሆን ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ይጽፋሉ፣ በሚጽፉበት ጊዜ መምህራን ደረጃ በደረጃ እየደገፉ የፅሁፍ ሥራቸውን እንዲያሳኩ ያግዛሉ፡፡ በዚህ የአፃፃፍ ዘዴውስጥ ተማሪዎች በራስ መተማመናቸው እየዳበረ፣ ጥሩ ጽሁፎችን የመፃፍ አቅማቸው እየጎለበተ ሲሄድ የመምህራን ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ራስን ችሎ በመፃፍ ዘዴደግሞ ተማሪዎች በሚያገኙት ልዩ ልዩ ድጋፍ አማካኝነት ራሳቸውን ችለው እንዲጽፉይደረጋል፡፡

ተማሪዎች መጻፍን በሚለማመዱበት ወቅት ሊከተሏቸው የሚገቡ ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህደረጃዎች በሚከተለው ቅደም ተከተል ውስጥ ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

1. ማሰብ፡- ፀኃፊዎች ሀሳብን የሚሰበስቡበት፣ አንባቢን የሚያስቡበት፣ አበይት ነጥቦችንየሚያቀርቡበት፣ ጊዜያዊ እቅዳቸውን የሚነድፉበት በአጠቃላይ ወደ ዋናው የጽህፈት ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ውስጥ ቢጋር ማውጣት ወሳኙ ጉዳይነው፡፡፡ በዚህ ርዕስ መምረጥ፣ የምንጽፍበትን ዓላማ መወሰንን የሚያካትት ነው፡፡

2. ማቀድ፡- የቢጋር ሰንጠረዥ መጠቀም፣ ሀሳብ ማመንጨት፣ የጽሁፉን ዓይነት/መዋቅር መወሰን፣ የሚፃፉትን ዋና ዋና ጉዳዮች መወሰን/ ርዕሰ ጉዳዩን ማጥበብ፣ ተደራሲንመለየት፣ መረጃ ማደራጀትና ማሰባሰብ፣ መረጃዎችን ማደራጀት፣ መረጃዎችን በየፈርጁ መመደብ ቅደም ተከተል መስጠትና እንደገና ማደራጀት የሚመለከት ነው፡፡ቢጋር በታላሚው ጽሁፍ ውስጥ ምን ምን ነጥቦች እንደሚካተቱ ጠቅለል ጠቅለል እያደረጉበስርዓት ማስፈር ነው፡፡ ይህ ቢጋር ከመጨረሻው ጽሁፍ በኋላ ሊታረሙ እንዲያውም ሊቀሩይችላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ሁለት አይነት የቢጋር አወጣጦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አንድ ጽሁፍ ከመፃፍ በፊትና የሁለተኛው ጽሁፍ ከተጠናቃቀ በኋላ የሚወጡ ቢጋሮች ናቸው፡፡ በማፍለቅጊዜ የተሰበሰቡ ሀሳቦች ይመረጡና በአጭር በአጭሩ በቢጋር ላይ ተደራጅተው ከሰፈሩ በኋላሀሳቡ እንዳይደባለቅበት በወገን በወገን ለመለየት፣ የተሰበሰበው ሀሳብ ያለቦታው እንዳይገባና የአስተሳሰብ ሂደቱን እንዳይገደብበት ይረዳዋል በማለት Richards (1990) ያብራራሉ፡፡

3. ማርቀቅ፡- ሁለተኛ የጽህፈት ደረጃ በቅድመ ጽህፈት የተመረጠውን ሀሳብ መልክ በማስያዝ በወረቀት የሚሰፍርበት ፡፡ ረቂቁን ከማርቀቅ ይነሳል፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት ቅርጾችንምይጠቀማል፡፡ እነዚህም ቅርፆች መግቢያ፣ ዋና አካል መደምደሚያ ናቸው፡፡ ይህ የሀሳብ አረጃጀት ቅርጽ በአብዛኛው በአጭርና በረጅም የጽሁፍ አይነት ያገለግላል፡፡

ሀ. መግቢያ፡- አንባቢን ከመጀመሪያው ለንባብ የሚያነሳሳ መሆን ይገባዋል፡፡ በእርግጥ መግቢያው የማንበብ ፍላጎትን የሚያነሳሳ ሳቢ ሊሆን ይገባዋል፡፡

ለ. ዋና አካል፡- የዋና አካል ተግባሩ በመግቢያው የተጠቀሱትን ነጥቦች ማጠናከር ነው፡፡ለምሳሌ፡- መዘርዝር፣ ምክንያት፣ ማብራሪያ፣ ምሳሌ መስጠትና ወዘተ… ነጥቦቹን የበለጠ ግልጽ እንዲሆኑና እንዲታወቁ ማድረግ ነው፡፡ በምሳሌው ስር የተዘረዘሩት ያለ መግቢያ በዋናውአካል ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ዋና አካል በአጭርም ሆነ በረጅም ጽሁፍ የማይቀር ነው፡

ሐ. መደምደሚያ፡- ጽሁፉ ማለቁን የምንገልጽበት ክፍል ነው፡፡ አንድ ፀሃፊ መደምደሚያ ሲጽፍ የተለያዩ ቴክኒኮችን ይጠቀማል፡፡ አመልካች ቃላት በመጠቀም የመጨረሻዎቹን አረፍተ ነገሮች አካሄድ በመለወጥ ምስያ በመፍጠር እና ወደ መግቢያው በመመለስ መደምደም ይቻላል፡፡

4. መከለስ፡- በዚህ ደረጃ ጠቅላላ የክለሳ ንባብ የሚደረግበት በመሆኑ ተደራሲያኑ ያለምንም ችግር ጽሁፉን አንብበው ሀሳቡን እንዲያደንቁ ለማድረግ የሚስተካከል ነገር

ካለየሚስተካክልበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ፀሃፊው ለአንባቢው ያስቸግራሉ የሚላቸውን ቃላት በመምረጥ፣ የአረፍተ-ነገሮችን አደረጃጀት በማስተካከል አስተዋጽኦ መስጠትየሚፈለገውን ሀሳብ በተገቢው ቦታ መቅረብ አለመቅረቡን የሚመለከትበት ነው፡፡ መከለስ የመጀመሪያውን ረቂቅ እንደገና ማንበብ፣ ፅሁፍን ለቡድን አባላት በመስጠት እንዲከልሱማድረግ፣

5. እንደገና መጻፍ፡- ማሻሻያ ማድረግ የተከለሰውን ረቂቅ እንደገና ማንበብ፣ ሁሉም ዓረፍተነገሮች የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ፊደላትን፣ የአፃፃፍ ስርዓትንና ስርዓተ ነጥቦችንማስተካከል፣ በትክክልና በተገቢው ቦታ ያልገቡትን፣ ቃላት መቀየርና አስተካክሎ መጻፍንየሚያካትት ነው፡፡

6. ወደህትመት መውሰድ፡- የወጣለት ጽሁፍ መጻፍ፣ የመጨረሻ ቅጂ ማዘጋጀትና የተፃፈውንአሳትሞ ለአንባቢያን ማድረስ የሚሉ ደረጃዎችን የሚያከትት አቀራረብ ነው፡፡
ከላይ ከቀረቡት ሁለት የጽህፈት ክሂል አቀራረቦች ወይም ከውጤት ተኮር አቀራረብና ከሂደትተኮር አቀራረብ አጥኝዋ ይዛው ከተነሳችው ምርምርና ከተጠኝዎቹ የጽህፈት ክሂል ደረጃ አንፃር ተመራጭ የሚያደርገው ሂደት ተኮር አቀራረብን ነው፡፡ ምክንያቱም ውጤት ተኮር የመምህሩ ሚና ይበዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለሚጽፉት ድርሰት አብዛኛውን ጊዜ ርዕስ የሚመርጠው መምህሩ መሆኑ እንዲሁም ተማሪዎቹ ከስህተት እንዲማሩ አለመፍቀደና የመጨረሻው ውጤትላይ ማተኮሩ አሁን ካለንበት የመማር ማስተማር ዘዴ ጋር ተጣጥሞ አይሄድም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከላይ በተገለፀው መልኩ ተማሪዎችን የምናስጨንቃቸው ከሆነ የመጻፍ ክሂልን ከነአካቴው እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል፡፡

በመሆኑም የመጻፍ ክሂል ለአፊ ፊትም ይሁን ለኢ-አፊፊት ተመራጭ የሚሆነው ሂደት ተኮርአቀራረብ ነው፡፡

ምህንያቱ ምለመምህር ሳይሆን ለተማሪዎቹ ነፃነት ስለሚሰጣቸውና መጻፍን በሂደት እንዲያዳብሩ ስለ ሚያደርጋቸው፤ ድርሰትም ለመፃፍ ርዕስ እራሳቸው እንዲመርጡ እድሉን ስለሚሰጣቸው፤ የመምህሩ ጫና ስለማይበዛባቸው እንዲሁም ከስህተታቸው እንዲማሩ አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ፤ የመጻፍ ክሂል ፍላጎታቸው ከፍ ስለሚል በሂደት ከአንድ ደረጃ ወደሌላ ደረጃ በሄደ ቁጥር የተሻለ ፀሃፍያን እንዲፈጠሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም የዚህ

ጥናትምዋና አላማ ተጠኚዎቹ ያለባቸውን የመጻፍ ችግር በሂደት የሚቀርፉበትን መንገድ መጠቆምና ጥሩ ፀሃፊ እንዲሆኑ መንገዱን ማመላከት ስለሆነ ሂደታዊ አቀራረብ ከዚህ ጥናት ጋር ስለ ሚሄድ በአጥኝዋ ተመራጭ ነው፡፡

በሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተገለጹትችቶች ሂደት ተኮር አቀራረብ እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት መፃፍን ለማስተማር የተሻለ አቀራረብ ሆኖ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኝ ቢሆንም ደካማ ጎን እንዳለው የተለያዩአስተያየቶች ተሰንዝረውበታል:: ከአስተያየቶቹ መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን እንመልከት:: የሂደት ተኮር አቀራረብ ለሰዋስው እና መዋቅር አነስተኛ ትኩረት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይበፅሁፍ ለሚገኝ የመጨረሻ ውጤት የሚሰጠው ግምት አነስተኛ ነው:: መፃፍን በሂደት አቀራረብ የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች በየግላቸው የራሳቸውን ውስጣዊ ችሎታእንዲጠቀሙ ከማበረታታቸውም በላይ ትክክለኛነትን ችላ ይላሉ:: , ሂደታዊ የመፃፍ ትምህርትአቀራረብ ሌላው ድክመቱ ሙሉ በሙሉ ነፃ መፃፍን ተግባራዊ በማድረግ የተማሪዎች የመፃፍችሎታ ይዳብራል የሚል አካሄድን መከተሉ ነው (Atikin,1996)::

ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ መፃፍን በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከተላቸው የማስተማሪያ ስልቶች አሉታዊ ጫና አላቸው:: ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ብዙ ረቂቆች እንዲጽፉ የሚሰጠው ትኩረት በየጊዜው ለሚጽፉት ጽሁፍ በተገቢው ሁኔታ የሚያዘጋጃቸው አይደለም:: በሌላ በኩል ለብጤ እርማት የሚሰጠው ከፍያለ ትኩረት ተማሪዎች ለራሳቸው ችሎታያላቸውን ግምት ዝቅ ያደርገዋል:: እንዲሁም በመፃፍ ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎችጥሩ በሚጽፉት ተማሪዎች ዘንድ ተለይተው እንዲታወቁ ስለሚያደርግ ስነልቦናዊ ጫናያስከትላል (Horwitz,1986)፡፡

### 2.2..3. ዘውግ ተኮር መጻፍን ማስተማሪያ አቀራረብ

ተማሪዎችን የተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶች ማስተማር የበለጠ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው ይችላልከሚለው አተያይ ጋር በተያያዘ፣ ዘውግ ተኮር መጻፍን ማስተማሪያ ስልት በ1980 ዎቹ ውስጥ የበለጠ ታዋቂነትን እያገኘ መምጣት ጀምሯል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶችን እያጠኑ ሲሄዱ በተጓዳኝነትም የተለያዩ መዋቅራዊና ቅርጻዊ የአጻጻፍ ስልቶችን በመረዳት በጽሁፋዊ ስራዎቻቸውም ውስጥ የተማሯቸውን የአጻጻፍ ስልቶች ተግባራዊ ሊያደርጓቸው ይችላሉ፡፡ይሁን እንጅ ይህን ሀሳብ የሚቃወሙ ወገኖች እንደሚሉት ጀነር አቀራረብ የተለያዩ የመጻፍ አይነቶች እንዴት የተለያዩ የአጻጻፍ መዋቅሮችን እንደሚሹ ለተማሪዎች ከማስተማር

አኳያ ስኬታማ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ምሁራን በዚህ አቀራረብ መሳሪያነት እውነተኛ ጽሁፎችን በክፍል ውስጥ ማስተዋወቅ በመቻሉ፣ የቀረቡት የተለያዩ የመጻፍ ማስተማሪያ አቀራረቦች የየራሳቸው የሆኑ ጥንካሬዎች ቢኖሯቸውም በአንጻሩ የየራሳቸው ድክመቶችም እንዳሉባቸው በተለያዩ ምሁራን (Brown, 1994, Badger & White, 2000) ተጠየቃዊ በሆኑ ማስረጃዎች በመገለጹ ምክንያት፣ ምሁራን ከአንድ በላይ የመጻፍ ማስተማሪያ አቀራረቦችን በማቀናጀት ተከታዩን የመጻፍ ማስተማሪያ አቀራረብ በአማራጭነት ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡

## 2.3 የተነሳሽነት ምንነት

Brown (2000:160) የተነሳሽነት ምንነትን ከሚከተሉት እይታዎች አንጻር ብያኔያቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ከባህሪያውያን እይታ አኳያ፡- ተነሳሽነት አንድን ተግባር ለማከናወን ማጠናከሪያ በመስጠት ምላሽ እንዲሰጥ ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ከአዕምሮታውያን አኳያ፡- በዚህ እይታ መሰረት ተነሳሽነት የሚመነጨው ከራሱ ከግለሰቡ ነው፡፡

ከግንባታውያን አኳያ፡- ይህ እይታ በማኅበራዊ አውድ እንዲሁም በግለሰቦች ምርጫከላይ የተመሰረተ ነው፡፡

በአጠቃላይ በሶስቱ መካከል ያለውን የተነሳሽነት እይታዎችን Brown (2000:160) በሚከተለው መልኩ ያስቀምጡታል፡፡

**ሰንጠረዥ 1.1 ፡- ከተነሳሽነት አንጻር ባህሪያውያን፣ አዕምሮታዊያን እና ግንባታውያንያ ላቸው እይታ**

| ባህሪያዉያን | አእምሮታዉያን | ግንባታዉያን |
|---|---|---|
| የማጠናከሪያ(ሽልማት)በመስጠት ላይ ያተኩራል | በግለሰቡ ፍላጎት ላይ ይመሰረታል | ማህበራዊ አዉድ ላይ ይመሰረታል |
| በዉጫዊ ሁኔታወች ወይም ግለሰቦች ቁጥጥር ስር ነዉ | ዉስጣዊ በመሆኑ በግለሰቡ ይመራል | ዉስጣዊ ሆኖ በተራክቧዊ ሁነቶች ላይ ይመሰረታል |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ ተነሳሽነት የሚፈጠርበትን መንገድ በተመለከተ በሶስቱ እይታ ምን እንደሚመስል ያሳያል፡፡ይህም በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ሲታይ ለተማሪው ማበረታቻ

ወይም ናማጠናከሪያ እየሰጠን የምናስተምረው ከሆነ በባህሪያውያን እይታ ተነሳሽነቱ ከፍተኛ እየሆነ እንደሚሄድ የሚያመለክት ነው፡፡ በሌላ መልኩ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ያለምንም ውጫዊ ተጽዕኖ በግለሰቡ ውስጣዊ ፍላጎት ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል የሚሉት ደግሞአዕምሮታውያን ናቸው፡፡ በተጨማሪም በግንባታውያን አተያይ ተማሪው በቋንቋ ትምህርትሂደት ባለው ውስጣዊ ተጽዕኖ እና በሚያከናውነው ማህበራዊ ተራክቦ በተነሳሽነቱ ላይበአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

ተነሳሽነት ከሚመነጭባቸው ከላይ ከቀረቡት ሶስት መንገዶች መካከል ይህ ጥናት የግንባታውያን አተያይ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የማኅበረ ባህላውያንገጽታ የሆነውን የግንባታውያን ንድፈ ሀሳብን ጥናቱ የተከተለ በመሆኑ ነው፡፡

## 2.4 የተነሳሽነት ዓይነቶች

ምሁራን የተነሳሽነት ዓይነቶችን በተለያየ መንገድ ሲከፍሏቸው ይታያል፡፡ Brown (2000:164) በመጥቀስ የተነሳሽነት ዓይነቶችን በሁለት ከፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡ እነሱም ውስጣዊ እና ውጫዊ ተነሳሽነት ናቸው፡፡

ውስጣዊ ተነሳሽነት፡- ውስጣዊ ተነሳሽነት ያለው የቋንቋ ተማሪ ታላሚውን ቋንቋ የሚማረው በተማረው ቋንቋ አንዳች ጥቅምን ለማግኘት ፈልጎ ወይም ሌላ ከበስተጀርባው የሚገፋፋውኃይል ኖሮ ሳይሆን፣ ቋንቋውን በመማሩ ከሚሰማው ውስጣዊ እርካታ በመነሳት በግሉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን ለማከናወን ጥረት የሚያደርግበት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የተነሳሽነትዓይነት ተማሪው ከውስጡ ከሚመነጭ ፍላጎት በመነሳት በታላሚው ቋንቋ የትምህርት ሂደት ላይ ተሳታፊ የሚሆንበት ነው፡፡

ውጫዊ ተነሳሽነት፡- በውጫዊ ተነሳሽነት ተማሪው ቋንቋውን የሚማረው ከውስጡ በመነጨስሜት ሳይሆን፣ የሌሎችን ድጋፍ ወይም ማበረታቻ በመፈለግ ነው፡፡ ይህ የተነሳሽነት ዓይነትበዋነኝነት የሚመሰረተው በውጫዊ ድጋፍ በመሆኑ የተነሳ ማበረታቻ እና እገዛ ለተማሪው የማይደረግለት ከሆነ በትምህርቱ ሂደት የመዳከም ሁኔታን ያሳያል፡፡ጥምረታዊ ተነሳሽነት ከራስ በሚመነጭ ፍላጎት ሳይሆን፣ ቋንቋውን የሚማረው በአስገዳጅ ሁኔታዎች ወይም በመማሩ የሚያገኘውን ጥቅም በማሰብ ነው፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች መካከልም ቋንቋውን ተምሮ ሥራለመያዝ፣ ፈተና ለማለፍ፣ ጉብኝቶችን ለማድረግ፣ ወዘተ… የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 2.5 የተነሳሽነት መገለጫዎች

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተነሳሽነት የሚለው ስነ ልቦናዊ ጽንሰ ሀሳብ ሲታሰብ በውስጡተያይዘው የሚነሱ ሌሎች ስነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች አሉ፡፡ Zimmerman & Bandura (1994) Pajares & Johnson (1996), እንደሚገልጹት ግለብቃት፣ ግለ ግንዛቤ እና ግለ መር ከተነሳሽነት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ መገለጫዎች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህን ሶስት ስነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች ምንነታቸውን በተመለከተ እንዲሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

### 2.5.1 ግለ ብቃት (Self Eficacy)

ግለ ብቃት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለመለካት ከሚያስችሉ የስነ ልቦና ገጽታዎችውስጥ አንዱ ነው (Bandura:1986 እና Pajares: 2003):: ግለ ብቃት የሚለውን የስነልቦና ጽንሰ ሀሳብ የተለዩ ምሁራን ልዩ ልዩ ብያኔዎችን ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡ ከእነዚህም መካከል Bandura (1986) እንደሚገልጹት ግለ ብቃት አንድን ተግባር በሚፈለገው መልኩ ከመፈጸም አኳያ የሚሰጥ ግለሰባዊ ውሳኔ ነው፡፡ ሰለዚ ግለ ብቃት አንዱ የተነሳሽነት ገጽታ ሲሆን፣ ተማሪዎች ቀደም ሲል ካከናወኗቸው ልዩ ልዩ የመጻፍ ተግባራት ተነስተው፣ በሂደት ከሚያሻሽሉት የመጻፍ ችሎታ አንጻር አለኝ ብለው ሊግልጹት የሚችሉት ችሎታ ነው፡፡

### 2.5.2 ግለ መር (Self Regulation)

ግለ መር ሌላኛው የተማሪዎችን የተነሳሽነት ደረጃ ለመለካት የሚያስችል እና የተነሳሽነት ውጤትን የሚያመለክት የስነልቦና ገጽታ ነው፡፡ ምሁራንም ስለምንነቱ በተመለከተ ሀሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡ Zimmerman (2008:166) እንደሚገልጹት ተማሪዎች በተለያዩ ዕለታዊ ገጠመኞች/ክንውኖች ያገኟቸውን አቅሞች (ቃላዊ አመለካከቶች) ወደ ስነ ትምህርታዊ ችሎታ ለመለወጥ ጥረት የሚያደርጉበት ነው፡፡

ተማሪዎች የግለ መር ክህሎቶች በቋንቋ ትምህርት የሚሰሯቸውን ተግባራት በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ይጠቁማሉ እንደማለት ነው፡፡በአጠቃላይ ከምሁራኑ ከተሰጡት ብያኔዎች መረዳት የሚቻለው ግለ መር ፣ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት ራሳቸውን የሚጠይቁበት እና የሚገመግሙበት ተግባር ሲሆን፣ በዚህ ሂደት ውስጥም ዓላማ አንስቶ አደራጅቶ እስከመገምገም ድረስ ልዩ ልዩ ሂደቶችን ያልፋሉ፡፡

### 2.5.3 ግለ ግንዛቤ (Self Concept)

ግለ ግንዛቤ እና ግለ ብቃት የሚሉት ሥነ ልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት ይስተዋልባቸዋል፤ ሆኖም ዕይታቸው የተለየ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ። ከእነዚህም መካከል Pajares and Schunk (2001) እንደሚገልጹት ግለ ግንዛቤ በጥቅል አስተሳሰባዊ እምነቶች ላይ ትኩረት ሲያደርግ፣ ግለ ብቃት ግን ሊለኩ የሚችሉ ዝርዝር ዓላማዎችን ከማከናወን አንጻር የሚታይ ነው። በተመሳሳይ Pajares (2003) እንደሚያስረዱት ግለ ግንዛቤ ተማሪዎች ለራሳቸው ያላቸውን አጠቃላይ ግምት የሚወስኑበት ሲሆን፣ ግለ ብቃት ግን ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ካሉ ዝርዝር ዓላማዎች/ተግባራት አንጻር ያላቸውን ችሎታ የሚተነብዩበት ነው፡ስለዚህ ግለ ብቃት፣ ግለ ግንዛቤ እና ግለ መር የሚሉት ስነልቦናዊ እሳቤዎች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የየራሳቸው ፋይዳ አላቸው። እነዚህም ጽንሰ ሀሳቦች የተለያዩ ቢሆንም፣ከተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ከፍተኛ መሆኑ ያመሳስላቸዋል። ስለዚ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለመለካት ሶስቱም ስነ ልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ተወስደው ተግባር ላይ ሊውሉ ችለዋል።

## 2.6 ተነሳሽነት ከመጻፍ ክሂል ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ

የተማሪዎች ተነሳሽነት በተሻለ ቁጥር የመጻፍ ችሎታቸውም ከፍ እያለ እንደሚሄድ፣ እንዲሁም በተቃራኒው የተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት እየቀነሰ በሄደ ቁጥር በመጻፍ ችሎታቸው እንደሚቀንስ ነው።

## 2.7 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር በተዘዋዋሪ ወይም በቀጥታ መንገድ ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ማመልከት ነው::ሰሎሞን (1991) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ድግሪ መሙያ "የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂ የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል:: የደረሱበት ውጤትም በመምህራን የማስተማር ዘዴ እና በተማሪዎች የመጻፍ ስትራቴጂ መካከል ክፍተት መኖር መምህሩ የሚከተለው የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች በተፈጥሮ ያላቸውን በመፃፍ ስትራቴጂ የሚያሳድግላቸው አለመሆኑን ጠቅሰዋል::አስቴር (1998) "የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ " በሚል ርዕስ በአራት የአዲስ አበባ መስተዳደር ትምህርት ቤቶች ጥናት ያካሄዱ ሲሆን የጥናታቸው ውጤት የሚያመለክተው

መምህራን መፃፍን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ በማፃፍ ሳይሆን በአብዛኛው ስነልሳናዊ ዕውቀቶችን ለማስጨበጥ  ትኩረት በመስጠት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል::

ስዩም(1988)  ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ (Process Approach) በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ላይ ያለዉ ተግባራዊነት በሚል ጥናት አካሂደዋል:: የጥናቱ አላማ የተማሪዎች የጽሑፍ ክሂል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ የህን ደረጃ ለማሳደግ ሂደታዊ የድርሰት አጻጻፍ ዘዴን በማሰተማሪያነት መጠቀም እንዳለበት ጠቁመዋል::

ተመስገን (2001) "የ11ኛ ክፍል መምህራን የመፃፍ ክሂል ማሰተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ" በሚሌ ርዕስ ግምገማ አካሂደዋል:: የጥናቱ ዓላማ በሀዲያ ዞን በሾኔ መሰናድ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ያለውን ግንኙነት በመፈተሽ የመምህራን የመፃፍ ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎችን የድርሰት መፃፍ ብልሀት መመርመር ነው:: በጥናቱ የተገኘው ውጤት በመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ እና በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሀት መካከል ተዛምዶ አለመኖሩን ጠቁመዋል::

ሶፍያ (2002) "በዳሞት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ድርሰትን ለማስተማር ሂደት ተኮር የማስተማር ስልት ያለውን ተግባራዊነት መፈተሸ" ላይ ግምገማ አካሂደዋል:: የጥናቱ ዓላማ የሂደት ተኮር የድርሰት ትምህርት አቀራረብ ያለውን ተግባራዊነት መፈተሽነው:: በጥናቱ የተገኘው ውጤት ሂደት ተኮር የድርሰት ትምህርት አቀራረብን በማወቅ እና በአግባቡ ተጠቅሞ የማስተማር ክንውን የሚካሄድበት አለመሆኑን እና የመምህራን ትኩረት ለተማሪዎች ስነልሳናዊ ዕውቀትን ለማስጨበጥ የታለመ በቃላት እና ሀረጋት ፍቺ እናአጠቃቀም ላይ ያተኮረ እንጂ እነዚህን ስነልሳናዊ ዕውቀቶች ተጠቅመው ሀሳባቸውን በፅሁፍመግለፅ የሚችልበት የማስተማሪያ ዘዴ አለመሆኑን ጠቁመዋል::

አማረ (2010) ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ (በዘጠነኞ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት)::የጥኔቱ አላማ ተግባር ተኮር የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል የሚናረውን ተጽዕኖ ለመፈተሽ ነው::

ቦሰና(2013) ሂደት ተኮር አቀራረብ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ እና ግለ ብቃትን ለማሳደግ ያለው

አስተዋጽኦ በአሰረኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ አላማ ሂደታዊ ዘዴ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ና ግለ ብቃትን ለማሳደግ ያለው አስተዋጽኦ መፈተሸ ነው።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥናታዊ ስራዎች የመፃፍ ክሂል ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች፣ የማስተማር ስነዘዴ ትግበራ፣ የመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴ እና ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር ባለው ተግባራዊነት ላይ በመመስረት የቀረቡናቸው። ከዚህ ጥናታዊ ስራ ጋር ያላቸው አጠቃላይ ዝምድና ማዕከላዊ ነጥባቸው ከመፃፍክሂል ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት በክለሳ ድርሳናት ውስጥ የሚቀርቡበትአንዳንድ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ሊኖረቸው ይችላል ተብሎይታሰባል።ይህ ጥናት በዋናነት ከነዚህ ጥናቶች የሚለየው ከትኩረት አቅጣጫው፣ ከአጠናን ስልቱ አንፃር ሰፊ ልዩነት አለው። በተጨማሪም ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ፣ የተተኳሪ መጠን ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣የጥናቱ ዘመን እናዓላማ ከቀደምት ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል። ይህ ጥናት ለ9ኛ ክፍልተማሪዎች የሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን የሚሞክር ከመሆኑም በተጨማሪከቦታ፣ ከጊዜ፣ ከትኩረት አቅጣጫ እና ከሙከራዊነቱ አንፃር ከቀደምት ጥናቶቹ ይለያያል።

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማው ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ እና ተነሳሽትን መፈተሽ ነው።ይህ ጥናት በዋናነት መጠናዊ የምርምር ዘዴ (Quantitative method) ላይ የተመሰረተ ሆኖ ገላጭ የመረጃ አተናተን ስልትን የተከተለ ነው።ይህንን አላማ ለማሳካት የባለ ሁለት ቡድን ቅድመ እና ድህረ ፈተናን መሰረት ያደረገ ከፊል ሙከራዊ  የ ጥናት ንድፍ ን የተከተለ ነው።

## 3.2 የናሙና አወሳሰድ

ጥናቱ በጉራጌ ዞን በገ/ጉ/ወ/ወረዳ በጅማ ወለኔ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተካሄደ ነው። በዚህ ወረዳ ስድስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ሲሆን በአመች የንሞና ዘዴን በመጠቀም የጅማ ወለኔ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመርጧል። ት/ቤቱ የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ በዚህ ት/ቤት የምትሰራ በመሆኗ በቅርበት ሆና መረጃ ለመሰብሰብ አመች ሆኖ በመገኘቱ ነው። በጥናቱ የተካተቱት በ2015 ዓ.ም በት/ቤቱ ተመዝግበው የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ተማሪዎች ናቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ አራት ክፍሎች ያሉ ሲሆን ጥናቱ ሙከራዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለ በመሆኑም በአንድ መምህርት ከሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በተራ እጣ ናሙና ዘዴ ሁለት ክፍሎች እንዲመረጥ ተደርጓል።ለጥናቱም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት ተማሪዎቹ ለጥናቱ በቂ  መረጃ ያስገኛሉ ተብሎ በመታመኑ ነው። የአመራረጥ ሂደቱ በት/ቤቱ በአንድ መምህርት በመማር ላይ ካሉ የአራት ክፍል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በቀላል የእጣ ናሙና ስልት ለተመረጡ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል።ተጠኝዎቹም ከላይ በተገለፀው መንገድ ተለይተው ከታወቁ በኋላ የመፃፍ ትምህርቱን በመደበኛው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በተጨማሪም በሳምንት ሁለት ጊዜ ለሁለት ሰዓታት ያክል እንዲሰጡ እና እንዲለማመዱ ተደርጎል።የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎቹም በተመረጠላቸው ግዜ መሰረት ለአራት ሳምንት እንዲለማመዱ ተደርገዋል።

## 3.3 የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት የመረጃ መሠብሰቢያ ሆኖ ጥቅም ላይ የሚውሉት ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው።

### 3.3.1 ፈተና

በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት የዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪ ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታቸውን ለመለካት በአጥኝዋ ቅደመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ተዘጋጅቶ በመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባር ላይ ውሏል። ፈተና ሁለት ተግባራትን የያዘ ነው ።የመጀመሪያው ቅድመ ፈተና ሲሆን ዋነኛ አላውማውም ተማሪዎች ከጥናቱ በፊት ከመፃፍ ክሂል አንፃር ያላቸው የችሎታ ደረጃ ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ሲባል ነው። ሁለተኛው ድህረ ፈተና ነው። የዚህ ፈተና ዋነኛ አላማ ደግሞ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በሂደታዊ የትምህርት አቀራረብ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች አሁን በተለመደው የማስተማሪያ አቀራረብ ከተማሩ በኋላ የመፃፍ ክሂላቸው መሻሻል አለመሻሻሉን ለማረጋገጥ ነው።

### 3.3.2 የፅሁፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት የተከናወነው የፅሁፍ መጠይቅ አላማ ሂደት ተኮር የመፃፍ ክሂል አቀራረብ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ያመጣውን ውጤት ለመፈተሽ ታስቦ ተካሂዷል። ሙከራዊ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የመፃፍ ትምህርትን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲሆን በመቀጠል ደግሞ በሂደታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ለመፃፍ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ታስቦ ነው።

## 3.4 የትግበራ ሂደት

በዚህ ጥናት ለሙከራ ቡድኑም ሆነ ለቁጥጥር ቡድኑ የማስተማሪያ መሳሪያ በመሆን ያገለገለው በ2004 ዓ.ም የተዘጋጀው መማሪያ መፃፍ ውስጥ ለመፃፍ ልምምድ የቀረቡ ይዘቶችን መሰረት በማድረግ ነው። በዚህ መማሪያ መፃፍ ውስጥ የቀረቡት ተግባራት የተመረጡበት ምክንያት ሌላ አዲስ የማስተማሪያ መሳሪያ ሲዘጋጅ በማስተማሪያ መሳሪያው መለያየት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ ተላውጦዎችን ለመቆጣጠር ታስቦ ነው።

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በአጥኝዋ ከተዘጋጁ በኋላ በመምህራን እና በአማካሪ እንዲገመገሙ ተደርጓል። በመቀጠልም ርዕሶችን ለተጠኝ ተማሪዎች በማቅረብ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ለፅሁፉ ርዕስነት ቅድሚያ የሚሰጧቸውን በደረጃ እንዲጠቁሙ ተደርጓል።

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋሉት ቅደመ ልምምድ እና ድህረ ልምምድ ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ነቸው። የመተንተኛ ዘዴዎችን በተመለከተ በቅድመ ትምህርትም ሆነ በድህረ ትምህርት የተገኙ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት ንጽጽር እንዲሁም

እያንዳንዱ ቡድን በተናጠል በቅድመ እና በድህረ ፈተና የተገኘውን ውጤት ለማነፃፀር በዳግም ልኬት ናሙና ቲቴስት ውጤት ተሰልቷል፡፡

## 3.6 የጥናቱ ስነምግባራዊ ሁኔታ

ለጥናቱ የሚውሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያመች ዘንድ በቅድሚያ ከአዲስ አበባ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር እና አስተዳደር አካላት ትብብር እንዲያደርጉ ተጠይቆ ፈቃደኛነት ከታወቀ በኋላ ለጥናቱ ከተመረጡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር በመሆን የጥናቱን አላማ በማስረዳት ለምርምሩ ፈቃደኛ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1. የውጤት ትንተና

ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና ተነሳሽነትን ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት በፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች በሂደት ተኮር ዘዴ የመፃፍትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደረጉ በኋላ ድርሰት የመፃፍ ችሎቸው ይሻሻላል? በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት ደግሞ በሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች ከልምምድ በኋላ ለመፃፍ ተነሳሽነት ላይ ለውጥ ያሳይ ይሆን? የሚሉት መሠረታዊ የምርምሩ ጥያቄዎች ተተንትነዋል፡፡

በዚህ መሠረት በቅድሚያ በተተኳሪ ትምህርት ቤቱ በአንድ መምህር ስር በመማር ላይ ከሚገኙ አራት ክፍሎች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በቀላል የዕጣ ንሞና የተለዩ የሁለት ክፍል ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ተሰልቷል፡፡ እነዚህ በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ የተመረጡት የሁለት ምድብ ተማሪዎች የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ሆነው ተመድበዋል፡፡ ሆኖም ግን የተመረጡት የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖችን አማካዩን ብቻ በማየት በተሻለ መልኩ ተመጣጣኝ የመጻፍ ችሎታ እንዳላቸው ለመፈተሽ እንዲረጋገጥ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበውም ሰንጠረዥ ይህን የሚመለከት ይሆናል፡፡

**ሰንጠረ ዥ 1 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ የመጻፍ ፈተና ችሎታ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ- ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የፐዋጋ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቁጥጥር | 50 | 31.25 | 11.05 | 98 | 3.275 | 0.64 |
| 2 | የሙከራ | 50 | 33.70 | 12.10 | | | |

ሰንጠረዥ 1 የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታፈተና ያላቸውን አማካይ ውጤት ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ ላይ እንደ ሰፈረው በባዕድ ናሙናቲ ቴስት ታስቲክስ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት (31.25) ስሆን የሙከራ ቡድኑ የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ (33.70) ተስተውሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ከልምምድ በፊት የመጻፍ ችሎታቸው ተቀራራቢ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ልምምድ ፈተና መደበኛ ልይይት (11.05) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ መደበኛ ልይይጥ ደግሞ (12.10) ነው፡፡ በመሆኑም አማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የመጻፍ ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡ ልዩነታቸውን በስታስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤታቸው መካከል ጉልህልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመለየት መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት ፍተሻ ተሰልቶ ውጤቱ የቲ ዋጋ (3.275) የP ዋጋ (0.64) አሳይቷል፡፡ ይህም በመጻፍ ችሎታ ረገድ በሁለቱም ቡድኖች አማካዮች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም የ P ዋጋ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) በልጦ ተገኝቷል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ያስከመዘገቡት ውጤት በንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 2 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ የመጻፍ ፈተና ችሎታ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ- ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የፐዋጋ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቁጥጥር | 50 | 38.06 | 10.03 | 98 | 7.45 | 0.000 |
| 2 | የሙከራ | 50 | 55.51 | 11.14 | | | |

በሰንጠረዥ 2 እንደቀረበው በድህረ ትምህረት የመጻፍ ችሎታ ፈተና የሙከራዊ ቡድኑአማካይ ውጤት (55.51) ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (38.06) በልጦ ተገኝቷል፡ በመሆኑም

የሙከራ ቡድኑ ያስመዘገበው 55.51 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ያስመዘገበው ደግሞ 38.06 ነው፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለውየሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተና ያስመዘገበው አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱ ነው፡፡ይህ ደግሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል በመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ያስመዘገቡት መደበኛ ልይይት በሚታይበት ጊዜየቁጥጥር ቡድኑ (10.03) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ (11.14) ነው፡፡ የአማካይውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የመጻፍ ችሎታ ልዩነት ማሳየት ከባድ ነው፡፡ልዩነታቸውን በስታስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱም አማካይ ውጤቶች መካከልጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት አማካኝነት ተሰልቶ የቲዋጋ (7.45) የP ዋጋ (0.000) ሆኗል፡፡ ይህም በቡድኖች መካከል ድህረ ትምህርት የመጻፍችሎታ ፈተና መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም የP ዋጋ (0.000) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሶ በመገኘቱ ነው፡፡ ይህ ውጤት የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑየመጻፍ ችሎታ ውጤት

**ሰንጠረዥ 3 የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ የመጻፍ ችሎታ ንጽጽር በዳግም ናሙና ቲ ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የTዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅድመ ፈተና | 50 | 31.25 | 11.05 | 6.957 | 49 | 0.000 |
| 2 | ድህረ ፈተና | 50 | 38.06 | 10.03 | | | |

በሰንጠረዥ 3 እንደቀረበው የድህረ ትምህርት ድርሰት የመጻፍ ፈተና አማካይ ውጤት(38.06) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (31.25) የሚበልጥ ይመስላል፡፡ በመደበኛ ልይይትም በኩል ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት ከቅድመፈተና መደበኛ ልይይት ያነሰ ቢመስልም ሁሉቱም ግን የተማሪዎች ውጤት ከአማካዩ

ሰፊ ልዩነት እንዳለው የሚያመላክቱ ናቸው፡፡የአማካዩችን ልዩነት ግን እንዲሁ በማየት ልዩነት አለ ወይም የለም በሚል ብቻ መተማመን ስለማይቻል ይህንኑ በቲ-ቴስት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የስታቲስቲክስ ስሌቱ በ50 የነፃነት ደረጃ የ ቲ ዋጋ (6.957) የP ዋጋ (0.000) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱምአማካዩች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች አማካይመካከል ጉልህ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለመፈተሽም የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተግባር ላይ ውሏል፡፡ በሁሉም ረገድ የተሰራው ስሌት ውጤቱ በሰንጠረዥ 1.3ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4 የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመና ድህረ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ንጽጽር በዳግም ናሙና ቲ -ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የፒዋጋ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅድመ ፈተና | 50 | 33,70 | 12.10 | 49 | 14.583 | 0.000 |
| 2 | ድህረ ፈተና | 50 | 55.51 | 11.14 | | | |

በሰንጠረዥ 4 እንደቀረበው የድህረ ትምህርት ድርሰት የመጻፍ ፈተና አማካይ ውጤት(55.51) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (33.70) የሚበልጥ ይመስላል፡፡ በመደበኛ ልይይትም በኩል ድርሰት በመጻፍ ችሎታ የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት ከቅድመ ፈተና መደበኛ ልይይት ያነሰ ቢመስልም ሁሉቱም ግን የተማሪዎች ውጤት ከአማካዩ ሰፊልዩነት እንዳለው የሚያመላክቱ ናቸው፡፡የአማካዩችን ልዩነት ግን እንዲሁ በማየት ልዩነት አለ ወይም የለም በሚል ብቻ መተማመን ስለማይቻል ይህንኑ በቲ-ቴስት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የስታቲስቲክስ ስሌቱ በ50 የነፃነት ደረጃየቲ ዋጋ (14.583) የፒ-ዋጋ (0.000) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱም አማካዩች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ለውጡ የመጣው በሂደትተኮር ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን

ሊጠቀም ይችላል፡፡የጥናቱ ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ በሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚማሩተማሪዎች ከልምምድ በኋላ ለመፃፍ  ተነሳሽነትላይ ለውጥ ያሳይ ይሆን? የሚል ነው፡፡ለዚህም በፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት እና በዳግም ልኬትናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡ ውጤቱም በሚከተሉት ሰንጠረዦች የተመለከተውን ይመስላል፡፡

ለዚህም በፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና ውጤቱም በሚከተሉት ሰንጠረዦች የተመለከተውን ይመስላል፡፡

**ሰንጠረዥ5 የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ተነሳሽነት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ንጽጽር በዳግም ናሙና ቲ-ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የፐዋጋ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቁጥጥር | 50 | 13.27 | 3.27 | 98 | 6.082 | 0.000 |
| 2 | የሙከራ | 50 | 20.1 | 7.668 | | | |

በሰንጠረዥ 5 እንደቀረበው የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ተነሳሽነትያላቸውን አማካይ ውጤት ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ ላይ እንደሰፈረው በባዕድ ናሙና ቲ ቴስትስታስቲክስ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ልምምድ ተነሳሽነትአማካይ ውጤት (13.27) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ደግሞ (20.1) ተስተውሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ከልምምድ በፊትያላቸው ግለ ብቃት ተቀራራቢ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም የቁጥጥርቡድኑ የቅድመ ልምምድ ተነሳሽነት መደበኛ ልይይት (3.27) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ መደበኛልይይጥ ደግሞ (7.668) ነው፡፡ በመሆኑም አማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው ተነሳሽነት ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡ ይህም በመጻፍ ችሎታ ረገድ በሁለቱም ቡድኖች አማካዮች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም የ P ዋጋ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05)

በልጦ ተገኝቷል።በዚህ መሰረት በቅድመ ትምህርት ተነሳሽነት የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከታወቀ በኋላ የሙከራዊ ቡድን በሒደት ተኮር ዘዴ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለመደው የመማር ማስተማር ዘዴሲማሩ ቆይተው ድህረ ትምህርት ተነሳሽነት በሁለቱ ቡድኖች ያስመዘገቡት ውጤት በንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት ተተንትኖ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ 6 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የድህረ ተነሳሽነት ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የፐዋጋ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቁጥጥር | 50 | 18.425 | 3.89 | 98 | 15.68 | 0.000 |
| 2 | የሙከራ | 50 | 26.3 | 6.446 | | | |

በሠንጠረዥ 6 እንደቀረበው በድህረ ትምህረትተነሳሽነት የሙከራዊ ቡድኑ አማካይ ውጤት(26.3) ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (18.425) በልጦ ተገኝቷል። በመሆኑም የሙከራቡድኑ ያስመዘገበው 26.3 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ያስመዘገበው ደግሞ 18.425 ነው። ሁለቱምቡድኖች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ተነሳሽነት ያስመዘገበው አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱ ነው። ይህ ደግሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ተነሳሽነት አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል። ሁለቱም ቡድኖች ያስመዘገቡት መደበኛ ልይይት በሚታይበት ጊዜ የቁጥጥር ቡድኑ (3.89) ሲሆን የሙከራቡድኑ ደግሞ (6.446) ነው። የአማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የተነሳሽነት ልዩነት ማሳየት ከባድ ነው። ልዩነታቸውን በስታስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱም አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በባዕድ ናሙናቲ ቴስት አማካኝነት ተሰልቶ የቲ ዋጋ (15.68) የP ዋጋ (0.000) ሆኗል። ይህም በቡድኖችመካከል ድህረ ተነሳሽነት መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል። ምክንያቱም የP ዋጋ(0.000) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሶ በመገኘቱ ነው። ይህ ውጤት የሚያሳየው

የሙከራቡድኑ ተነሳሽነት የተሻለ መሆኑን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የሂደታዊ የመጻፍ ትምህርትአቀራረብ ዘዴ የተማሩት ውጤታማ መሆናቸውን ነው፡

**ሰንጠረዥ 7 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ተነሳሽነት ንፅፅር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የፐዋጋ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅደመ የጽሑፍ መጠይቅ | 50 | 13.75 | 3.27 | 49 | 0.615 | 0.000 |
| 2 | ድህረ የጽሑፍ መጠይቅ | 50 | 18.425 | 3.89 | | | |

ሰንጠረዥ 7 መረዳት እንደሚቻለው የድህረ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት(18.425) ከቅድመ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (13.75) የሚበልጥይመስላል፡፡ መደበኛ ልይይትንም በተመለከተ የድህረ ተነሳሽነት መደበኛ ልይይት ከቅድመ ተነሳሽነት መደበኛ ልይይት ያነሰ መሆኑን ከሰንጠረዥ 1.7 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሰንጠረዡ የተመለከተውን በቅድመ ተነሳሽነት በድህረ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት መካከል ያለውንልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በውጤቱ እንደ ተመለከተው በ50 የነፃነት ደረጃ የቲ ዋጋ (0.615) የPዋጋ (0.000) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ አማካዩች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ በሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች ከልምምድ በኋላ ለመፃፍ ተነሳሽነትላይ አዎንታዊ ተፅእኖ እንዳለው ተጨማሪ መረጃይሰጣል፡፡

ሰንጠረዥ 8 **የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረተነሳሽነትንፅፅር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት**

| ተ,ቁ | ቡድን | የናሙና ብዛት | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የፐዋጋ | የባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅደመ የጽሁፍ መጠይቅ | 50 | 20.1 | 0.402 | 49 | 0.808 | 0.000 |
| 2 | ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ | 50 | 22.3 | 0.446 | | | |

ከሰንጠረዥ 8 መረዳት እንደሚቻለው የድህረ ተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት(22.3) ከቅድመ የጽሑፍ አማካይ ውጤት (20.1) ይበልጣል፡፡ መደበኛ ልይይቱ ከቅድመናድህረ ትምህረት የጽሁፍ መጠይቅ ዝቅተኛ የመደበኛ ልይይት ውጤት መገኘቱን ከሰንጠረዡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሰንጠረዥ 1.8 የተመለከተው በቅድመ የጸሑፍ መጠይቅ እና በድህረየጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ያለውን ልዩነት በስታስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥየዳግም ልኬታ ናሙና ቲ ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በ50 የነፃነት ደረጃ የቲ ዋጋ (0.808) የP ዋጋ (0.000) ሆኗል፡፡ ይህ የሚያሳየው በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ እና በድህረ የጽሑፍ መጠይቁ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህም የሒደት ተኮር መጻፍንማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑንመረዳት ይቻላል፡፡በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው ከሰንጠረዥ 1.8 መረዳት እንደሚቻለው የድህረ ተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት(22.3) ከቅድመ የጽሑፍ አማካይ ውጤት (20.1) ይበልጣል፡፡ መደበኛ ልይይቱ ከቅድመናድህረ ትምህረት የጽሁፍ መጠይቅ ዝቅተኛ የመደበኛ ልይይት ውጤት መገኘቱን ከሠንጠረዡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሰንጠረዥ 8 የተመለከተው በቅድመ የጸሑፍ መጠይቅ እና በድህረ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ያለውን ልዩነት በስታስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የዳግም ልኬታ ናሙና ቲ ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በ50 የነፃነት ደረጃ የቲ ዋጋ (0.808) የP ዋጋ

(0.000) ሆኗል፡፡ ይህ የሚያሳየው በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ እና በድህረ የጽሑፍ መጠይቁ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህም የሒደት ተኮር መጻፍን ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው፡፡ በቅድመትምህርት ፈተናና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህልዩነት ($p<0.05$) ታይቷል፡፡ በተጨማሪም ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ እንዳለው በትንተናው የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡ በዚህም በቅድመ ተነሳሽነትና ድህረ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ታይቷል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራርያ

የዚህ ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና ተነሳሽትን ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያለውን ፋይዳ፣ ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን በመጻፍ ችሎታ ላይ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱን፣ ለመፈተሽ መረጃዎች በገላጭና በድምድሚያዊ ስታቲክሶች ተተንትነዋል፡፡በውጤት ትንተናው በቅድሚያ ምላሽ የተሰጠው ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው፡፡ በሰንጠረዥ 2 እንደ ተመለከተው ከቅድመ ትምህርት ፈተና በልጦ የተገኘው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በስታቲክስ ጉልህ ($P<0.05$) ሆኖ መገኘቱ የሂደት ተኮር የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ያሻሻለ መሆኑን አመላክቷል፡፡

ሌላኛው ተማሪዎች ከመጻፍ ችሎታቸው ጋር በተያያዘ አለኝ ብለው የሚያምኑት ብቃት ነው፡፡ እነዚህም የብቃት አይነቶች ከመጻፍ ትምህርት ጋር የተያያዙ ንዑሳን ዓላማዎችን ከመጠቀም ጋር የሚያያዙ ሲሆን እነሱም፣ ቢጋር መንደፍን፣ድርሰትን አድራጅቶ መጻፍን፣ሥርዓተ ነጥብን በተገቢው ቦታ መጠቀምን፣ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት አጠቃቀምን፣ በትክክል መጻፍን፣ ሰዋስውን ጠብቆ የመጻፍ ተግባር ማከናወንን፣ ወዘተ… የሚጠይቁ ናቸው፡፡

በዚህ የጥናት ሂደትም የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት እንዲፈተሽ ተደርጓል፡፡በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ እና ድኅረ የጽሑፍ መጠይቅ ያስመዘገቡት ውጤት ከተነሳሽነት አኳያ ሲሰላ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ጉልህ ልዩነት እንዳለ ይጠቁማል፡፡ይኸውም በጥንድ ናሙና ቲ ቴስት

ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ጉልህ ልዩነት ማምጣት እንደቻሉ ነው። ይህ ውጤት እንደሚያመለክተው ልምምዱ ቢቀጥል የበለጠ ጠንካራ ሊሆን እንደሚችል አጥኚዋ ታምናለች። ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ቀደም ሲል ከአጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ተነሳሽነ አንጻር ከተገኘው ውጤት በመነሳትም ጥናቱ ካስቀመጣቸው ጥያቄዎች በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ከተነሳሽነት አንጻር ጉልህ ልዩነት መኖሩ ተቀባይነትን አግኝቷል።

በአጠቃላይ በሂደት ተኮር ድርሰት የመጻፍ ችሎታን የሚያጎልበት መሆኑን በክለሳ ድርሳኑ ላይ Raymis (1983), Richards (1990) የምርምር ውጤቶች አመላክተዋል። በዚህ ጥናት ውጤትም የሂደት ተኮር የማስተማር ዘዴ ችሎታንና በማሻሻል ተነሳሽነትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በአማካይ ውጤቱ አመላክቷል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፤ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች

## 5.1. ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ሂደት ተኮር ድርሰት የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል የሚኖረውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው።የጥናቱ ማጠቃለያ ሂደታዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ የማሳደግ ሁኔታ የሚፈጥር የበለጠ ተማሪ ተኮር አቀራረብ ነው:: ይህ ዘዴ ተማሪዎች በዓላማና ቅርፅ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲገነዘቡና በተለየ ሁኔታ ለቅድመ መፃፍ፣ንድፍ፣ ክለሳና አርትኦትን ለመፃፍ ተግባር እንዲጠቀሙ የሚፈቅድ ነው:: ጥናቱ ሲካሄድ የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎች ለማነቃቃት የሂደታዊ ዘዴ  አካሄዶች ስራ ላይ ውለዋል ። ለዚህ ጥናት ግብዓት የሆኑ መረጃዎች በቅድመ፣ በሂደትና መጨረሻ ላይ ተሰብስበዋል። ከተጠኚዎቹ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል። በዚህ ክፍል ዋና ዋና አካሄዶች እና ግኝቶች ቀርበዋል።የዚህ ጥናት ዓላማ የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር የተሻለ አስተዋፅዖ ይኖረው ወይም አይኖረው እንደሆነ ማረጋገጥ ነው። በዚህም ምክንያት ተመራማሪዋ  የምርምር ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ የጥናቱን አካሄድ በሚከተለው ንድፍ መሰረት አከናውናለች።

የድርሰት አጻጻፍ ክሂልን ትምህርት በማጠናከር በኩል የተገኘው ምላሽ ከፈተናው ና ከሚጠይቁ በተገኘው ውጤት ለመረዳት እንደተሞከረው ተማሪዎች  የተሰጣቸውን ትምህርት በተግባር ለማዋል ችለዋል።

ተማሪዎች በሂደታዊ ዘዴ ድርሰት እንዴት እንደሚጽፉ ትምህርት ከማግኘታቸው በፊት በቂ ድርሰት አጻጻፍ ተነሳሽነት እንዳልነበረባቸው ከሚጠይቅ በተገኘው መረጃ መረዳት ሲቻል ትምህርት እንዳልነበራቸው ከመጠይቅ በተገኘው መረጃ መረዳት ሲቻል ትምህርቱን ካገኙ በኋላ ግን የክሂል ለውጥ ማሳየታቸው ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ለመረዳት ተችሏል። የታየውም ጉልህ ልዩነት በአጋጣሚ ሳይሆን ስለ ሂደታዊ ዘዴ የተሰጣቸው ትምህርት የተደረገላቸው እገዛና ያደረጉት ልምምድ አንደሆነ የውጤቱ ከፍተኛነት ይጠቁማል።

1 የሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን በመጠቀም የተማሪዎችን የመጻፍ ችልታ ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ መፈተሽ፤

2. የሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን በመጠቀም በተማሪዎች የመፃፍ ትምህርት ተነሳሽነት ላይ ሊያመጣየሚችለው ለውጥ መፈተሽ፡፡

ጥናቱን ለማከናወን በቀላል የንሞና ዘዴ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማለትም የጅማ ወለኔ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ሲሆን፣ በዚህ ትምህርት ቤት ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል ከ9ኛ ክፍል አንድ የቁጥጥርና አንድ የሙከራ ቡድኑ የተወሰደ ሲሆን ለሙከራ ጥናቱ የ9ኛ ሀ ክፍል 50 ተማሪዎች ለቁጥጥር ቡድኑ የ9ኛ ለ ክፍል 50 ተማሪዎች ተወስደዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እንዲሁም ለቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው የመፃፍ ማስተማሪያ ስልት እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የአንድ ሰዓት ርዝማኔ ያለው ሆኖ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ኖሮት የሙከራው ጥናት ለአራት ሳምንት ተከናውኗል፡፡በጥናቱ ዙሪያ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተመራማሪዋ ሁለት የምርምር ዓላማዎችን ነድፋለች፡፡እነዚህን አላማዎች ለማሳካት የ9ኛ ክፍል ሁለት ምድብ የ9ኛሀ እና የ9ኛለ ተመርጠው የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ተደርገው ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በዚህ ሂደት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ከተጠኚዎቹ የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ አስችለዋል፡፡ ከነዚህ መካከል የመጀመሪያውና ዋነኛው የቅድመ ትግበራ እና የድኅረ ትግበራ ፈተና ውጤት ንፅፅር ነው፡፡ በመሆኑም የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት የቅድመ ትግበራ ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሙከራ ቡድኑ በሂደታዊ ዘዴ አቀራረብ ለአራት ሳምንታት የመፃፍ ክሂል ትምህርት እንዲከታተሉ ተደርገው በመጨረሻ የድኅረ ትግበራ ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ቀሪው ለቁጥጥር ና ሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን በዚሁ የተሰበሰቡ መረጃዎች በዳግም ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

አጠቃላይ የጥናቱ ግኝትም በሚከተለው መልክ ቀርቧል፡፡የመጀመሪያው የምርምሩ ዓላማ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች ልምምድ ካደረጉ በኋላ ድርሰት የመጻፍ ችሎታቸው ይሻሻል ይሆን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ነው፡፡ ይህን የምርምር ዓላማ መሰረት በማድረግ የተገኘው መረጃ መሰረት ተቃኝቷል፡፡ በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል የተከሰተ ልዩነት መኖር አለመኖሩን

ለማረጋገጥ የቅድመ እና ድህረ ትግበራ ፈተናዎች ውጤት ንጽጽር ነው፡፡የቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤቶች እንደሚያመለክቱት የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ከማሳደግ አኳያ የተሻለ ውጤታማ ነው፡፡ በመሆኑም የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችግር ለማቃለል አማራጭ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ሆኖ ሊታሰብ ይችላል፡፡ የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል አንፃር ውጤታማ መሆኑን እናጤናለን፡፡ በዳግም ናሙና ቲ ቴስት የተካሄደውን የውጤት ትንተና የሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናው ይልቅ በድህረ ፈተናው የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህም የሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

ለሁለተኛው የምርምሩ ዓላማ በሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች ከልምምዱ በፊትና በኋላ ለመፃፍ ክሂል ያላቸውን ተነሳሽነ መፈተሸ ነው፡፡ በዚህ የምርምር ዓላማ የቁጥጥር ቡድኑ እናየሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰት በመፃፍ ያላቸው ተነሳሽነት ተመዝኗል፡፡ ለዚህ የምርምር ዓላማ እንዲረዳ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊትና ጥናቱ ከተካሄደ በኋላ ስላላቸው ተነሳሽነት ለመረዳት ለሙከራ ቡድኑ እና ለቁጥጥር በድኑ ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ቀርቧል፡፡

የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በመተግበሩ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰት በመፃፍ ረገድ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርጓል:: ከዚህ በተጨማሚ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርት ለመማር እንዲነሳሱና በራስ የመተማመን ፍላጎታቸው ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡እንዲሁም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በግልፅ እንዲወያዩ፣እንዲጠያየቁና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አግዟቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህ አቀራረብ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰት ስለመፃፍ ያላቸው ተነሳሽነት አዎንታዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ተማሪዎች እርስ በርስና ከመምህር ጋር የፈጠሩት ግንኙነት በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎችም በዚህ አቀራረብ ተጠቃሚ መሆናቸውን፣ ይህ አቀራረብ የመጀመሪያቸው መሆኑንና በዚህ አቀራረብ መማር ከጀመሩ ወዲህ ድርሰት የመፃፍ ፍላጎታቸው እንደተነሳሳ በጽሑፍ መጠይቅ ምላሻቸው አስረድተዋል፡፡ በልምምድ ወቅት የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ለመምህሩም ሆነ

ለተማሪዎች ጠቃሚ መሆኑን ለማየት ተችሏል። በመሆኑም ለተማሪዎች የተሟላ የመማር ልምድ ለመፍጠር፣ በመፃፍ ትምህርት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ነው።

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት ውጤቶች እንዳመለከቱት የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከመፃፍ ትምህርት አንፃር ሁሉን ችግር የሚፈታ ባይሆንም ተማሪዎች መፃፍን በመማር ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረታታ ሆኖ ታይቷል። ከዚህም ሌላ ተማሪዎች እርስ በርስ ሀሳብን እንዲለዋወጡ፣ዕውቀታቸውን እንዲያካፍሉ፣ እድል የሚሰጥ ነው። ይህ አቀራረብ ትምህርቱን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ፍላጎት ለሌላቸው መምህራን የተለያዩ አጋጣሚዎችን የሚፈጥር መሆኑ ታይቷል።

## 5.2. መደምደሚያ

ይህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ነው። ከዚህ አንፃር ለጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የቀረበው የመፃፍ ትምህርት በተማሪዎቹ የመፃፍ ክሂል መሻሻል ላይ የተሻለ መሆኑ ተረጋግጧል::

1. ይህ ጥናት የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታን ከማሳደግ አኳያ የተሻለ መሆኑን አረጋግጧል።

2. የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ድረሰት በመጻፍ ረገድ የተለያዩ ሞዴል ፅሑፎችን በማምጣት ተማሪዎች እንዲለማመዱ በማድረግና በልምምዱ ወቅት ተማሪዎች እርስ በራሳቸው እንዲሁም በተማሪዎችና በመምህሩ መካከል የመረዳዳትና መረጃ የመለዋወጥ ሂደትን በማጠናከር በተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ አመለካከት ላይ አዎንታዊ ለውጥ መፍጠሩን ለማጤን ተችሏል።

## 5.3. የመፍትሔ ሀሳቦች

ይህ ጥናት የሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል መሆኑን አሳይቷል። በመሆኑም ከዚህ ውጤት በመነሳት አቀራረቡ ተግባራዊ መሆን ይችል ዘንድ በተመራማሪዋ እይታ መተኮር አለባቸው የተባሉ ነጥቦች ቀጥሎ ተዘርዝረዋል።

1. የሂደታዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር ጥሩ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

2. መምህራን የሂደታዊ አቀራረብን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የሚጠበቀው ትምህርታዊና ማህበራዊ ስኬት እንዲመጣ ተማሪዎች አዲሱን አቀራረብ በሚገባ እንዲረዱት እና በትምህርቱ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ በቂ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

3. መምህራን ጥሩ ግንዛቤ ኖሯቸው በክፍል ውስጥ በተገቢው ሁኔታ መተግበር እንዲችሉ የሚያደርጋቸው በቂ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል

4.መምህራን የማስተማሪያ ዘዴውን የሚተገብሩ ዋነኛ አካላት ናቸው፡፡በመሆኑም የማሰተመሪያ ዘዴው በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ላይ የፈጠረውን ተጽዕኖ በማሰብ አተገባበሩ ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች


ሀናታምራት:: (2003) :: "በሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ጽህፈት ክሂል ኮርስ የአቀራረበና አተገባበር ፍተሻ::" አዲስ አበባ ለአማርኛ ማስተማር ማስተ ርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ/::

ማረው አለሙ:: (1996)፡፡ በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን ዮሀንስ:: (1991):: የተማሪዎችን የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ እስትራቴጂ የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞሽ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ/ያልታተመ

ስዩም ከበደ:: (1988)::"ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/::

ሰይድ ይመር:: (1993):: "በ9ኛ ክፍል ለአማርኛ መማሪያ መፃህፍት የቀረቡት የጽህፎች ትምህርቶችና የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ የመማር ማስተማር ሂደት ግምገማ በሰባት አዲስ አበባ ቤቶች ናሙናነት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/::

ሶፍያ ሙሀመድ:: (2002):: "በዳሞት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍልድርሰትን ለማስተማር ስልት ያለውን ተግባራዊነት መፈተሸ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ /ያልታተመ/::

ቦሰና መለሰ:: (2013):: ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ እና ግለ ብቃትን ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ በአስረኛ ክፍል ተተኳሪነት::ጎንደር ዩኒቨርስቲ በአማርኛ ማስተማር ማስተር ድግሪ የቀረበ/ያልታተመ/::

ተመስገን ፈቀደ:: (2001):: "የ11 ክፍል መምህራን የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ::" (በሃዲያ ዞን በሾኔ መሰናድ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ (የተካሄደ ጥናት):: አዲስ አበባዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪማሟያ የቀረበ /ያልታተመ/

አለማየሁ ፀጋዬ:: (1986):: "የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፅሙ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ምንጮች ትንተና::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ /ያልታተመ/

አስቴር ሳሙኤል:: (1998):: የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

አማረ ተሾመ:: (2010)::ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ያለው ተጽኖ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)::

Atkinson, D. (2003). ''L2 Writing in the post process era, Introduction on.'' Jornal of Second Language Writing .12.3-15.

Al-Shourafa, A. (2012). The Effect of Motivation on Jordanian 10th grades Student' Writing skill in English. European Scientific Journal, 8(22), 235-247

Alamrew G/Mariam (2005) "A Study on the Perception of Writing, Writing Instruction and Students' Writing Performance." Addis Ababa University (Unpublished PhD Thesis).

Badger, R. and White, G. (2000) ''Product, Process and Gener: Approaches to Writing in EAP.'' (Electronic Version). ELT Jornal, 54(2), 153-160.

Bandura, A. (1986). Social Foundations of Thought and Action: a social cognitive theory. Englewood' Cliff, NJ: Prentice Hall.

Burden and Larson and Toonen (2005) Gaining In Dependence Through Collaboration: Using Partner or Small Group Conferences to Discuss Students' Drafts.

Brown, D. (2000). Principles of Language Learning and Teaching. New York: Addison Wesley Longman.

Brown (2001). Teaching by Principle: An Interactive Approach to Language Pedagogy. (2nd ed), New York: Addison wesly Longman,

Brown. H.D (1994). Principles of Language Learning and Teaching (4te ed), white plawns, NY: Addison wesley longman.

Byrne, D. (1988). Teaching Writing Skills. Longman: Longman Group UK Lmited

Burack, Boris. (1965.) " Composition: Why? What? How?" English Language Journal 54. pp.504,506.

Byrne,Dounn, 1991. Teaching Writing Skills. London: Longman Group UK Lerni Lmited.

Celce Murcia, M. (ed).(1991). Teaching English as a second or foreign language. Bosten: Heinle And heinle publisher.

Ebabu Tefera (2013). “A Study on Writing, Writing: Instruction, Student Perception and Writing Performance.” Addis Ababa University (Unpublished PhD Thesis

Ferris, D. (2003). “Responding to Writing.” In Kroll, B. (Ed.) ExploringThe Dynamics of Second Language Writing. (119-140). Cambridge:Cambridge Universit.

Hedge, T. (1988) Writing Resource Book for Teachers.Oxford: Oxford University

Horowitz, D.(1986), “process not prouct: Less than meets the eye” TESOL Quarterly. Process and the Gener Approach” (Electronic Version) Asian EFL Jornal. 7(2). John andlizsoars(1986)Headway students book Intermediate oxford Universit press

kroll (1991) Teaching writng in the ESL Context Teaching English ascond Language.ed

Lim, J. (2007). “Responding to Students Writing: Peer and Teacher Feedback.”Modern English ,Education, 8(2), 59-7 approach to teaching writing”. The English Teacher, 35, 75-85.

Mesfin Aberra (2013). “An Explanatory Study on the Implementation of the Process Approach to the teaching Learning of the Course Basic Writing Skills in the Case of Hawassa University.” Addis Ababa University (Unpublished PhD Thesis).

Mohamed, E. (2015). “University Students’ English Writing Problems: Diagnosis and Remedy.” International Journal of English Language Teaching, Vol.3, (3), 40-52. Murray DOnald (1982)Learning and Teahing Portsmouth Hesnman Enducationl Book’s

Nunan, D. (1989). Language Teaching Methodology: A Textbook for Teachers.London: Prentice Hall.

Pajares, F. (2003). Self-efficacy Beliefs, Motivation and Achievement in Writing: A Review of the Literature. Reading and Writing Quarterly ,Vol.19, 139-158.

Pajares, F, & Johnson, M. J. (1996). Self-efficacy beliefs in the writing of entering high school students: A path analysis. Psychology in the Schools, Vol.33, 163-175.

Pajares, F. and Schunk, D. H. (2001). “Self Belifes and School Success: Self Efficacy, Self Concept and School Achivement.” In R. Riding and S. Rayner (Eds.) Self Perception(PP.239-266) London :Ablex Publishing

Raymis, A. (1983).Techniques in the Teaching writing. New York: OUP.

Richards, J.C. (1990). The Language Teaching Matrix. Cambridge: CUP.Shunk, D. H

Tangerpermpoon, T. (2009). Integrated approaches to improve students writing skill for English major students. ABAC Journal, 28 (2), 1-9.

Wallace, T. and et al. (2004). Teaching Speaking, Listening and Writing. Belgium, Brussels International Burea of Education (IBE)

Yan, G. (2005). A Process Gener Model for Teaching Writing English Teaching Forum.

Zimmerman, B. (Eds). (1994). Self-regulation of learning and performance: Issues and educational applications. Hillsdale, NJ: Lawrence Erlbaum Associat

# አባሪዎች

**አባሪ ሀ, የቅድመ ትምህርት ድርሰት የመፃፍ ፈተና**

ለጅማ ወለኔ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ቅድመ ፈተና

ፆታ------------------------------- አድሜ ------------------------------ጊዛዊ መለያ ኮድ________________

መመሪያ:--የዚህ ቅድመ ፈተና ዋና አላማ ሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ነው፡፡ ስለዚህ የቀረበውን ርዕስ መሰረት በማድረግ በትዕዛዙ መሰረት መልስ/ሽ፡፡ለምታደርጉት ትብብር አጥኝዋ ልባዊ ምስጋና ታደርጋለች፡፡

1, <<ለተማሪዎች ጥሩ ውጤት ማምጣት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ልዩ ልዩ ገዳዮች>>በሚል ርዕስ አንድ አስረጂ ድርሰት ፃፍ/ፊ

**አባሪ ለ, የድኅረ ትምህርት ድርሰት የመፃፍ ፈተና**

በጅማ ወለኔ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ድህረ ፈተና

ፆታ------------------------------- አድሜ --------------------------ጊዛዊ መለያ ከባድ _______________

መመሪያ:--የዚህ ቅድመ ፈተና ዋና አላማ ሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ነው፡፡ እናም የዚህን ጥናት አላማ ማሳካት የሚቻለው እናንተ የምትጠየቁትን ጥያቄ በትክክል መመለስ ስትችሉ ነው፡፡

የቀረበውን ርዕስ መሰረት በማድረግ በትዕዛዙ መሰረት መልስ/ሽ፡፡ለምታደርጉት ትብብር አጥኝዋ ልባዊ ምስጋና ታደርጋለች፡፡

1,<<ለተማሪዎች ጥሩ ውጤት ማምጣት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ልዩ ልዩ ገዳዮች>>በሚል ርዕስ አንድ አስረጂ ድርሰት ፃፍ/ፊ

**አባሪ ሐ, በተማሪዎች የሚሞላ የተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ**

ፆታ----------------ዕድሜ--------------------------------------ጊዛዊ መለያ ኮድ _________________

ለጅማ ወለኔ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ፡፡

ውድ ተማሪዎች የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ ለአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል የላችሁን ተነሳሽነት ለመፈተሽ ነው። በውስጡም የተካተቱ የጥያቄዎች ቁጥር ብዛት 15 ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም በዚህ መጠይቅ ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ትክክለኛ ነው ብላችሁ የምታስቧቸውን ምላሾች በመምረጥ ለጥናቱ አላማ መሳካት የበኩላችሁን አስተዋጽኦ አንድታደርጉ በአክብሮት አጠይቃለሁ።

ማሳሰቢያ:-

- በመጠይቁ ላይ ስም አይጻፍም።

የቀረቡትን መጠይቆች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ የመረጣችሁትን ምላሽ በያዘው ቁጥር ስር የ√ ምልክት በማስቀመጥ ምላሻችሁን አመልክቱ ።

ምርጫዎች:-- 5, በጣም አስማማለሁ = 4, እስማማለሁ =3, መወሰን ያስቸግረኛል

2, አልስማማም =1, ፈጽሞ አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | እንድፅፍ የተሰጠኝ የመፃፍ ተግባር ጋር በቀጥታ የተዛመደ ፅሁፍ አፅፍለሁ። | | | | | |
| 2 | አምባቢወችን በማሰብ ፅሁፌን እፅፍለሁ። | | | | | |
| 3 | በምፅፍበት ጊዜ የተለያዩ አያያዦችን በትክክለኛ ቦታቸዉ እጠቀማለሁ። | | | | | |
| 4 | ለምፅፈዉ ፅሁፍ ተገቢዉን አስተዋጽኦ መንደፍ እችላለሁ። | | | | | |
| 5 | ከምፅፈዉ ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ዝርዝር ዓ.ነገሮች በደብተሬ ዉስጥ እጠቀማለሁ። | | | | | |
| 6 | በምፅፍበት ጊዜ የአማረኛ ፊደሎችን በትክክል እጠቀማለሁ። | | | | | |
| 7 | የሚሰጠኝን የመፃፍ ተግባራት ትክክለኛ የሰዋሰው ስርዓትን ተከትየ በጥንቃቄ እፅፍለሁ። | | | | | |
| 8 | በፅሁፌ ዉስጥ ተገቢዉ ስርዓተ ነጥብ በተገቢዉ ቦታ እጠቀማለሁ። | | | | | |
| 9 | በምፅፍበት ጊዜ ሰፊ አገልግሎት ያላቸዉን ቃላት እጠቀማለሁ ። | | | | | |
| 10 | ለመፃፍ የምፈልገዉን ሀሳብ በቅደም ተከተል በማስያዝና በማደራጀት እፅፍለሁ | | | | | |
| 11 | በምፅፈዉ ድርሰት ዉስጥ ከራሴ አተያይ አንፃር የምፈልገዉን ሀሳብ በተገቢው መልኩ አስተላልፍለሁ። | | | | | |
| 12 | በምፅፈዉ ድርሰት ዉስጥ ተገቢነት ያላቸው መግቢያና መደምደሚያ ሀሳብ እፅፍለሁ። | | | | | |
| 13 | በመፃፍ ትምህርት ጊዜ ማከናወን የሚጠበቁብኝን ቅድመ ሁኔታወች ጠንቅቄ ማወቄ ደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል። | | | | | |
| 14 | ከመፃፌ በፊት የምፅፍበትን ዕርሰ ጉዳይ የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ሀሳቦችን አፈልቃለሁ። | | | | | |
| 15 | ጽሁፌን ካጠናቀኩ በኋላ ለክፍል ጓደኞቼ በማሳየት አስተያየት እቀበላለሁ። | | | | | |

አማረ (2010) እና ቦሰና (2013) በመጥቀስ ከዘረዘሯቸው የጽሁፍ መጠይቆች ውስጥ 15ቱን ለዚህ ጥናት እንዲስማሙ ተደርገው የተወሰዱ።

## አባሪ መ. የቅድመና ድህረ ሙከራ ፈተና ውጤት

## በሁለት አራሚዎች የታረመው የተማሪዎች የቅድመና የድህረ ፈተና የቁጥጥር ቡድኑ ውጤት

| ተማሪ | | የቀድመ መከራ ፈተና ውጤት (ከ100%) | | | የድህረ ሙከራ ፈተና ውጤት (ከ100%) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፆታ | መለያ ኮድ | አራሚ 1 | አራማ2 | አማካይ ውጤት | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አማካይ ውጤት |
| ሴ | ለ1 | 29 | 25 | 27 | 41 | 42 | 41 |
| ወ | ለ2 | 29 | 29 | 29 | 45 | 40 | 42 |
| ወ | ለ3 | 31 | 29 | 30 | 34 | 30 | 32 |
| ሴ | ለ4 | 28 | 30 | 29 | 33 | 37 | 35 |
| ሴ | ለ5 | 44 | 44 | 44 | 54 | 51 | 53.5 |
| ወ | ለ6 | 25 | 21 | 23 | 32 | 34 | 33 |
| ሴ | ለ7 | 34 | 31 | 32.5 | 42 | 45 | 43.5 |
| ሴ | ለ8 | 30 | 35 | 32.5 | 47 | 43 | 45 |
| ወ | ለ9 | 37 | 35 | 36 | 42 | 47 | 45.5 |
| ወ | ለ10 | 35 | 30 | 32.5. | 40 | 44 | 42 |
| ወ | ለ11 | 37 | 35 | 36 | 38 | 34 | 36 |
| ወ | ለ12 | 31 | 28 | 29.5 | 36 | 33 | 34.5 |
| ወ | ለ13 | 35 | 39 | 37 | 44 | 48 | 46 |
| ወ | ለ14 | 44 | 43 | 43.5 | 49 | 47 | 48 |
| ወ | ለ15 | 22 | 26 | 24 | 31 | 33 | 32 |
| ወ | ለ16 | 32 | 34 | 33 | 33 | 35 | 34 |
| ሴ | ለ17 | 34 | 30 | 32 | 34 | 34 | 34 |
| ሴ | ለ18 | 31 | 31 | 31 | 31 | 33 | 32 |
| ሴ | ለ19 | 34 | 42 | 38 | 41 | 42 | 41.5 |
| ሴ | ለ20 | 28 | 31 | 29.5 | 35 | 31 | 33 |
| ሴ | ለ21 | 31 | 34 | 32.5 | 36 | 33 | 34.5 |
| ሴ | ለ22 | 30 | 34 | 32 | 47 | 43 | 45 |
| ሴ | ለ23 | 43 | 45 | 44 | 51 | 55 | 53 |
| ሴ | ለ24 | 35 | 31 | 36 | 38 | 35 | 36.5 |
| ወ | ለ25 | 23 | 27 | 25 | 30 | 30 | 30 |
| ወ | ለ26 | 27 | 25 | 26 | 26 | 27 | 26.5 |
| ወ | ለ27 | 37 | 32 | 33.5 | 35 | 31 | 33 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | ሰ28 | 29 | 23 | 26 | 38 | 30 | 34 |
| ወ | ሰ29 | 21 | 23 | 22 | 36 | 36 | 34 |
| ወ | ሰ30 | 35 | 31 | 33 | 38 | 35 | 36.5 |
| ሴ | ሰ31 | 41 | 45 | 43 | 60 | 58 | 58 |
| ወ | ሰ32 | 41 | 37 | 39 | 43 | 51 | 42 |
| ሴ | ሰ33 | 64 | 30 | 34 | 39 | 34 | 36.5 |
| ወ | ሰ34 | 31 | 31 | 31 | 36 | 32 | 34 |
| ወ | ሰ35 | 33 | 31 | 32 | 39 | 35 | 37 |
| ሴ | ሰ36 | 39 | 35 | 37 | 43 | 40 | 41.5 |
| ሴ | ሰ37 | 22 | 20 | 21 | 34 | 30 | 32 |
| ወ | ሰ38 | 28 | 32 | 30 | 34 | 40 | 37 |
| ወ | ሰ39 | 24 | 23 | 23.5 | 27 | 24 | 25.5 |
| ሴ | ሰ40 | 20 | 24 | 22 | 21 | 29 | 25 |
| ወ | ሰ41 | 27 | 33 | 30 | 33 | 35 | 34 |
| ሴ | ሰ42 | 35 | 32 | 33.5 | 48 | 44 | 46 |
| ሴ | ሰ43 | 31 | 31 | 31 | 41 | 39 | 40 |
| ወ | ሰ44 | 30 | 27 | 28.5 | 33 | 29 | 31 |
| ሴ | ሰ45 | 49 | 45 | 47 | 55 | 59 | 57 |
| ወ | ሰ46 | 44 | 40 | 42 | 52 | 56 | 54 |
| ወ | ሰ47 | 42 | 34 | 38 | 54 | 51 | 53 |
| ሴ | ሰ48 | 32 | 36 | 34 | 39 | 42 | 40.5 |
| ወ | ሰ49 | 25 | 28 | 27.5 | 45 | 49 | 47 |
| ወ | ሰ50 | 49 | 53 | 51 | 53 | 57 | 55 |

በሁለት አራሚዎች የታረመው የተማሪዎች የቅድመና የድህረ ፈተና የሙከራ ቡድኑ ውጤት

| ተማሪ | | የቅድመ መከራ ፈተና ውጤት (ከ100%) | | | የድህረ ሙከራ ፈተና ውጤት (ከ100%) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፆታ | መለያ ኮድ | አራሚ 1 | አራማ2 | አማካይ ውጤት | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አማካይ ውጤት |
| ወ | ሀ1 | 31 | 27 | 29 | 53 | 51 | 52 |
| ሴ | ሀ2 | 27 | 33 | 30 | 50 | 54 | 52 |
| ወ | ሀ3 | 31 | 27 | 29 | 57 | 53 | 55 |
| ወ | ሀ4 | 42 | 46 | 44 | 51 | 54 | 53.5 |
| ወ | ሀ5 | 25 | 21 | 23 | 55 | 51 | 53 |
| ወ | ሀ6 | 31 | 34 | 32.5 | 52 | 55 | 53.5 |
| ሴ | ሀ7 | 32 | 33 | 32.5 | 53 | 57 | 55 |
| ወ | ሀ8 | 37 | 35 | 36 | 57 | 52 | 54.5 |
| ወ | ሀ9 | 35 | 30 | 32.5 | 50 | 55 | 52 |
| ሴ | ሀ10 | 34 | 38 | 36 | 58 | 52 | 54.5 |
| ወ | ሀ11 | 28 | 31 | 29.5 | 56 | 53 | 56 |
| ወ | ሀ12 | 39 | 35 | 37 | 54 | 58 | 58 |
| ሴ | ሀ13 | 42 | 45 | 43.5 | 59 | 57 | 58 |
| ወ | ሀ14 | 22 | 26 | 24 | 53 | 61 | 57 |
| ሴ | ሀ15 | 35 | 33 | 34 | 51 | 55 | 53 |
| ወ | ሀ16 | 35 | 30 | 32 | 52 | 56 | 54 |
| ሴ | ሀ17 | 31 | 31 | 31 | 49 | 53 | 51 |
| ሴ | ሀ18 | 35 | 41 | 38 | 55 | 61 | 58 |
| ሴ | ሀ19 | 28 | 31 | 29.5 | 55 | 51 | 53 |
| ሴ | ሀ20 | 34 | 34 | 34 | 56 | 53 | 54.5 |
| ሴ | ሀ21 | 30 | 34 | 32 | 53 | 57 | 55 |
| ወ | ሀ22 | 49 | 43 | 46 | 59 | 55 | 57 |
| ወ | ሀ23 | 36 | 36 | 36 | 55 | 61 | 58 |
| ወ | ሀ24 | 23 | 26 | 24.5 | 48 | 52 | 50 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | ሀ25 | 24 | 28 | 26 | 56 | 52 | 54 |
| ወ | ሀ26 | 36 | 33 | 35.5 | 53 | 53 | 53 |
| ሴ | ሀ27 | 27 | 25 | 26 | 57 | 51 | 54 |
| ሴ | ሀ28 | 22 | 25 | 22 | 56 | 52 | 54 |
| ሴ | ሀ29 | 35 | 31 | 33 | 57 | 53 | 55 |
| ሴ | ሀ30 | 45 | 41 | 43 | 56 | 62 | 58 |
| ሴ | ሀ31 | 41 | 37 | 39 | 61 | 63 | 62 |
| ሴ | ሀ32 | 34 | 34 | 34 | 57 | 61 | 59 |
| ወ | ሀ33 | 32 | 30 | 31 | 58 | 60 | 59 |
| ሴ | ሀ34 | 34 | 30 | 32 | 65 | 69 | 67 |
| ሴ | ሀ35 | 35 | 39 | 37 | 63 | 60 | 61.5 |
| ወ | ሀ36 | 23 | 20 | 21 | 50 | 54 | 52 |
| ወ | ሀ37 | 30 | 30 | 30 | 54 | 60 | 57 |
| ወ | ሀ38 | 23 | 26 | 25.5 | 54 | 57 | 55.5 |
| ወ | ሀ39 | 24 | 20 | 22 | 51 | 49 | 50 |
| ወ | ሀ40 | 31 | 29 | 30 | 55 | 53 | 54 |
| ወ | ሀ41 | 33 | 36 | 34.5 | 54 | 58 | 56 |
| ወ | ሀ42 | 30 | 32 | 31 | 51 | 49 | 50 |
| ወ | ሀ43 | 28 | 31 | 29.5 | 51 | 51 | 51 |
| ወ | ሀ44 | 49 | 45 | 37 | 59 | 55 | 57 |
| ሴ | ሀ45 | 44 | 40 | 42 | 56 | 52 | 54 |
| ወ | ሀ46 | 41 | 35 | 38 | 54 | 52 | 53 |
| ወ | ሀ47 | 36 | 32 | 34 | 57 | 61 | 59 |
| ሴ | ሀ48 | 25 | 28 | 27.5 | 59 | 55 | 57 |
| ወ | ሀ49 | 49 | 53 | 51 | 66 | 61 | 63.5 |
| ሴ | ሀ50 | 25 | 29 | 27 | 51 | 49 | 50 |

## አባሪ ሠ,የቅድመ እና ድኅረ የመጻፍ ክሂል ፈተናዎችን ለማረም ተግባር ላይ የዋለው ሞዴል

ሂተን(1988፡146)ድርሰት ለማረም የሚያስችል የነጥብ አሰጣጥ

| | |
|---|---|
| 1.ይዘት | |
| 30-27ከእጅግ በጣም ጥሩ.......በጣም ጥሩ | ሰለ ርእሱ የተሟላ እውቀት ያዘለ፣በደንብ የተብራራ፣ ወዘተ |
| 26-22ከጥሩ.......አማካይ | ሰለ ርእሱ መካከለኛእውቀትያዘለ፣በበቂመረጃየቀረበ፣ወዘተ |
| 21-17ከደህና.......ደካማ | ስለ ርእሱ ውስን እውቀት ያዘለ፣ጥቂት ፋሬ ነገር በቻ ያለበት ፣ወዘተ |
| 1613በጣምደካማ | ሰለ እርሱ ምነም እውቀት የላዘለ፣በደንብ የልተብራራ፣ወዘተ |
| 2 .አደረጃጀት | |
| 20-18ከእጅግበጣም ጥሩ......... በጣም ጥሩ | ርቱዕ የሆነ አገላለጽ የሚታይበት፣ ሀሳቦች በግልጽ የቀረቡበት፣ ወዘተ |
| 17-14ከጥሩ........አማካይ | በወጉ ያልተደራጀና እንደነገሩ የቀረበ፣ይህም ሆኖ ግን ወናው ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት፣ ወዘተ |
| 13-10ከደህና........ደካማ | ርቱዕነት የማይታይበት፣ሀሳቦች የተምታቱበት፣ወይም የልተያያዙበት፣ወዘተ |
| 9-7በጣምደካማ | ምንም መልዕክት የሚያስተላልፍ፣ ሀሳቦች የተምታቱበት፣ወይም ያልተያያዙበት፣ወዘተ |
| 3.ቃላት | |
| 20-18ከእጅግበጣምጥሩ........በጣም ጥሩ | በሳል የሆነ፣ የተዋጣለት የቃላት፣ የአባባሎች መረጣና አጠቃቀምየሚታይበት፣ወዘተ |
| 17-14ከጥሩ.......አማካይ | በበቂ ደረጃ የቀረበ፣አልፎ አልፎ የቃላት (የአባባሎቸ)ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ሰህተት ቢታይበትም ምን ማለት እንደሆነ መገመት የሚቻልበት፣ ወዘተ |
| 13-10ከደህና .......ደካማ | በውስን ደረጃ የቀረበ፣ቃላት (አባባሎች) ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ተደጋጋሚ ስህተት የሚታይበት፣ ወዘተ |
| 9-7በጣምደካማ | የቃላት (አባባሎች) አጠቃቀም አውቀቱ በጣም አነስተኛ የሆነ ወዘተ |
| 4.የቋንቋ አጠቃቀም | |

| | |
|---|---|
| 25-22እጅግበጣምጥሩ......በጣም ጥሩ | ረቀቅ ያለ የቋንቋ አጠቃቀም በተዋጣለት ሁኔታ የቀረበ ፣ወዘተ |
| 21-19ከጥሩ..........አማካይ | የቋንቋ አጠቃቀሙ ተራ ሆኖ መልዕክቱ ግን በደንብ የሚተላለፍበት |
| 18-11ከደህና........ደካማ | ረቀቅ ባለም በተራ የቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የጎላ ችግር የሚታይበት |
| 10-5በጣምደካማ | በመሰረቱ የአረፍተ ነገር አመሰራረት ህግጋትን በወጉ ያላየ፣ወዘተ |
| 5. ሰርዓተ አጻጻፍ | |
| 5ከእጅግበጣምጥሩ......በጣም ጥሩ | የሥርዓተ አጠቃቀም ብቃቱ ከፍተኛ የሆነ፣ወዘተ |
| 4ከጥሩ...........አማካይ | አልፎ አልፎ የስርዓተ ነጥብና የሆሄያት ችግር የታየበት ወዘተ |
| 3ከደህና...........ደካማ | ተደጋጋሚ የሆነ የስርዓተ ነጥብና የሆሄያት አጣጣል ችግር የሚታይበት |
| 2በጣም ደካማ | የሥርዓተ አጻጻፍ አጠቃቀም ብቃት፣ የሌለው የሥርዓተ ነጥብ፣የፊደላት አጣጣል ችግር ጎልቶ የሚታይበት፣ ወዘተ |

አባሪ ሬ. በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና የድህረተነሳሽነትንለመፈተሽ የተሞላው የፅሁፍ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልሰ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቅድመ | ድህረ | ድምር | በመቶኛ | ቅድመ | ድህረ | ድምር | በመቶኛ |
| 1 | እንድጽፍ የተሰጠኝን የመጻፍ ተግባር ጋር በቀጥታ የተዛመደ ጽሑፍ እጽፋለሁ:: | 13 | 20 | 33 | 66 | 37 | 30 | 67 | 67 |
| 2 | አንባቢዎችን በመሰብ ፅሁፌን አጽፍለሁ | 15 | 18 | 33 | 66 | 35 | 32 | 67 | 67 |
| 3 | በመጽፋበት ጊዜ የተለያዩ አያያዦችን በተክክለኛ ቦታቸው አጠቀማለሁ:: | 14 | 19 | 33 | 66 | 36 | 31 | 67 | 67 |
| 4 | ለምጽፈው ጽሑፍ ተገቢውን አስተዋጽኦ መንደፍ እችላለሁ:: | 17 | 23 | 40 | 80 | 33 | 27 | 60 | 60 |
| 5 | ከምጽፈው ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ዝርዝር ዓ/ነገሮች በደብተሬ ውስጥ | 12 | 17 | 29 | 58 | 38 | 33 | 71 | 71 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እጠቀማለሁ:: | | | | | | | | |
| 6 | በምጽፋበት ጊዜ የአማርኛ ፊደሎችን በትክክል እጠቀመለሁ:: | 12 | 18 | 30 | 60 | 38 | 32 | 70 | 70 |
| 7 | የሚሰጠኝን የመጻፍ ተግባራት ትክክለኛ የሰዋሰውስርዓትንተከትዬበጥንቃቄአ ጽፋለሁ:: | 15 | 19 | 34 | 68 | 35 | 32 | 66 | 66 |
| 8 | በጽሁፌ ውስጥ ተገቢው ስረዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ አጠቀማለሁ:: | 14 | 20 | 34 | 68 | 36 | 30 | 66 | 66 |
| 9 | በምጽፍበት ጊዜ ሰፊ አገልግሎት ያላቸውን ቃላት እጠቀማለሁ:: | 11 | 17 | 28 | 56 | 39 | 33 | 72 | 72 |
| 10 | ለመጻፍ የምፈልገውን ሀሳብ በቅደም ተከተል በማስያዝ ና በማደራጀት እጽፋለሁ:: | 10 | 19 | 29 | 58 | 40 | 31 | 71 | 71 |
| 11 | በምጽፈው ድርሰት ውስጥ ከራሴ አተያይ አንጻር የሚፈለገውን ሀሳብ በተገቢው መልኩ አስተላልፋለሁ:: | 12 | 18 | 30 | 60 | 38 | 32 | 70 | 70 |
| 12 | በምጽፈው ድርሰት ውስጥ ተገቢነት ያላቸው መግቢያና መደምደሚያ ሀሳብ እጽፍለሁ:: | 12 | 16 | 28 | 56 | 38 | 34 | 72 | 72 |
| 13 | በመጻፍ ትምህርት ጊዜ ማከናወን የሚጠበቅብኝን ቅድመ ሁኔታዎች ጠንቅቄ መወቁ ደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል:: | 9 | 21 | 30 | 69 | 42 | 29 | 70 | 70 |
| 14 | ከመጻፌ በፊት የምጽፍበትን ርዕሰ ጉዳይ የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ሀሳቦች አፈልቃለሁ:: | 16 | 22 | 38 | 76 | 34 | 28 | 62 | 62 |
| 15 | ጽሁፌን ካጠናቀኩ በኋላ ለክፍል ጓደኞቼ በማሳየት አስተያየት እቀበላለሁ:: | 8 | 23 | 31 | 62 | 42 | 27 | 69 | 69 |

**አባሪ ሰ. በሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ተነሳሽነትን ለመፈተሽ የተሞላው የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቅድመ | ድህረ | ድምር | በመቶኛ | ቅድመ | ድህረ | ድምር | በመቶኛ |
| 1 | እንድጽፍ የተሰጠኝን የመጻፍ ተግባር ጋር በቀጥታ የተዛመደ ጽሑፍ እጽፋለሁ:: | 25 | 28 | 43 | 86 | 35 | 22 | 57 | 57 |
| 2 | አንባቢዎችን በመሰብ ፅሁፌን አጽፍለሁ | 14 | 24 | 38 | 76 | 36 | 26 | 62 | 62 |
| 3 | በመጽፋበት ጊዜ የተለያዩ አያያዦችን በተክክለኛ ቦታቸው አጠቀማለሁ:: | 16 | 25 | 41 | 82 | 34 | 25 | 59 | 59 |
| 4 | ለምጽፈው ጽሑፍ ተገቢውን አስተዋጽኦ መንደፍ እችላለሁ:: | 18 | 28 | 46 | 92 | 32 | 22 | 54 | 54 |
| 5 | ከምጽፈው ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ዝርዝር ዓ/ነገሮች በደብተሬ ውስጥ እጠቀማለሁ:: | 13 | 27 | 40 | 80 | 37 | 23 | 60 | 60 |
| 6 | በምጽፋበት ጊዜ የአማርኛ ፊደሎችን በትክክል እጠቀመለሁ:: | 14 | 25 | 39 | 78 | 36 | 25 | 61 | 61 |
| 7 | የሚሰጠኝን የመጻፍ ተግባራት ትክክለኛ የሰዋሰውስርዓትንተከትዬበጥንቃቄአጽፋለሁ:: | 17 | 28 | 45 | 90 | 33 | 23 | 55 | 55 |
| 8 | በጽሁፌ ውስጥ ተገቢው ስረዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ አጠቀማለሁ:: | 16 | 26 | 42 | 84 | 34 | 24 | 58 | 58 |
| 9 | በምጽፍበት ጊዜ ሰፊ አገልግሎት ያላቸውን ቃላት እጠቀማለሁ:: | 13 | 22 | 35 | 70 | 37 | 28 | 65 | 65 |
| 10 | ለመጻፍ የምፈልገውን ሀሳብ በቅደም ተከተል በማስያዝ ና በማደራጀት እጽፋለሁ:: | 12 | 23 | 35 | 70 | 38 | 27 | 65 | 65 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | በምጽፈው ድርሰት ውስጥ ከራሴ አተያይ አንጻር የሚፈለገውን ሀሳብ በተገቢው መልኩ አስተላልፋለሁ፡፡ | 13 | 24 | 37 | 74 | 37 | 26 | 63 | 63 |
| 12 | በምጽፈው ድርሰት ውስጥ ተገቢነት ያላቸው መግቢያና መደምደሚያ ሀሳብ እጽፍለሁ፡፡ | 14 | 22 | 36 | 72 | 36 | 28 | 64 | 64 |
| 13 | በመጻፍ ትምህርት ጊዜ ማከናወን የሚጠበቅብኝን ቅድመ ሁኔታዎች ጠንቅቄ መወቄ ደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል፡፡ | 11 | 22 | 34 | 66 | 39 | 28 | 67 | 67 |
| 14 | ከመጻፌ በፊት የምጽፍበትን ርዕሰ ጉዳይ የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ሀሳቦች አፈልቃለሁ፡፡ | 19 | 27 | 46 | 92 | 31 | 23 | 54 | 54 |
| 15 | ጽሁፌን ካጠናቀኩ በኋላ ለክፍል ጓደኞቼ በማሳየት አስተያየት እቀበላለሁ፡፡ | 10 | 24 | 34 | 68 | 40 | 26 | 66 | 66 |

በሂደት ተኮር ዘዴ የቀረበ የመጻፍ ትምህርት

## የዘጠነኛ ክፍል (የተማሪው )

የ2015 ዓ.ም

መግቢያ

ጽሁፍ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚታሰበው የተግባቦትዕውቀት እንዲኖራቸው በሚያስችል ሁኔታ መማር አለባቸው፡፡

ተማሪዎችዘጠነኛ ክፍል ከሚማሯቸው የቋንቋ ክሂሎች መካከል መጻፍ አንዱ ነው፡፡ መጻፍ የፊደላትን ቅርጽ ለይቶ ከመጻፍ ጀምሮ አዲስ ሃሳብን በማፍለቅ ቃላትንና ሐረጋትን አቀናጅቶ ዓረፍተ ነገርን፣ ዓረፍተ ነገሮችን አቀናጅቶ አንቀጽን በማዋቀር ሃሳብን በተደራጀና ግልጽ በሆነ መንገድ ለሌላው ማስተላለፍ የሚያስችል ሂደታዊ ተግባር ነው፡፡

በዚህ የዘጠነኛክፍል ትምህርት ደረጃ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በተለይም ድርሰት የመጻአስጣጥታቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉ ይዘቶች ተመርጠው የቀረቡ ሲሆን ከመማሪያ መጽሐፍ

የተወሰዱ ምንባቦችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ምንባቦቹ ከተማሪዎች ዕድሜ፣ አካባቢ፣ ፍላጎትና ደረጃ ጋር የተገናዘቡ ናቸው ተብሎ ታስቧል፡፡ ምንባቦቹን ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎች አስቀድመው ከተነሱት ነጥቦች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ሙከራ ተደርጓል፡፡

ሀ. የትምህርቱ ዓላማ

√ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡

√ ስለቀረበላችሁ ርዕስ ታስባላችሁ፡፡

√ ስለርዕሰ ጉዳዩ አስተዋጽኦ ትነድፋላችሁ፡፡

√ በተዘጋጀው አስተዋጥኦ መሰረት ረቂቅ ትጽፋላችሁ፡፡

√ የተየጻፈውን ረቂቅ ድርሰት በማንበብ የማስተካከል ሥራ ትሰራላችሁ፡፡

√ አስረጅ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡

ለ. ተግባራት

√ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀም

√ አስተዋጽኦ መንደፍ

√ ረቂቅ መጻፍና መከለስ

√ አስተካክሎ መጻፍ

√ አስረጅ ድርሰት መጻፍ

ሐ. የማስተማሪያ ዘዴዎች

√ ሂደት ተኮር መጻፍን ማስተማሪያ ዘዴ

√ ገለፃ

√ የቡድን ውይይት

መ. ግምገማ

√ የቡድን እርማት

√ በግል የሚጽፏቸውን ድርሰቶች ማረም

√ አስተዋጽኦ ነድፈው ረቂቅ አዘጋጅተው አስረጅ ድርሰት መጻፋቸውን ማረጋገጥ፣ ማረምና ማስተካከያ መስጠት

ሠ. ማጣቀሻ መጽሐፍ

አማርኛ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ዘጠነኛ ክፍል (2004)፡፡ የአል-ጉሬር አሳታሚ ናአሳታሚ ድርጅት፡፡ ዱባይ፡፡

ክፋል አንድ

አስረጅ ድርሰት

1. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን በመምረጥአስተዋጽኦአዘጋጁ፡፡

ሀ. ማርፈድ

ለ. ከትምህርት ቤት መቅረት

ሐ. የጥናት መርሃ ግብር

2. ያዘጋጃችሁትን ቢጋር ከጓደኞቻችሁ ጋር በመለዋወጥ፡-

ሀ. የተዘጋጀው ቢጋር የሃሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን አረጋግጡ፡፡

ለ. ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆኑን መርምሩ፡፡

ሐ. ስለመረመራችሁት ቢጋር ለጓደኞቻችሁ አስተያየት ስጡ፡፡

አስተዋጽኦ

አስተዋጽኦ ዋናውን ጽሑፍ ለመጻፍ፣ መንገድ ቀያሽ ወይም ትልም ነው፡፡

የአስተዋጽኦ ጥቅም ፦

√ ጽሑፉ በሚጻፍበት ጊዜ ከዋናው ሀሳብ ላለማፈንገጥ ይረዳል፡፡

## አስረጅ ድርሰት

አስረጅ ድርሰት ከድርሰት ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡ የአንድን ነገር ምንነት፣ አገኛኘት፣ ባህሪያት፣ ዓይነት፣ መጠን፣ ቅርፅ፣ አሰራር፣ ጠቀሜታ፣ ጉዳት ወዘተ. የሚያብራራ የድርሰት ዓይነት ነው፡፡ አንድን ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ነገር አስመልክቶ ምንድን ነው? ምን ማለት ነው? የተሰራው ከምንድን ነው? እንዴት ተሰራ? እንዴት እንደዚህ ሊሆን ቻለ? ምን ጉዳት ወይም ጥቅም አለው? ወዘተ. በሚል ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚሞክር የድርሰት ዓይነት ነው፡፡

1. ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ መሰረት በማድረግና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስለ አካባቢያችሁ የሚያስረዳ አንድ አስረጅ ድርሰት ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ፡፡ ለመጻፍ በቅድሚያ ርዕስ ምረጡ፡፡ በመረጣችሁት ርዕስ ዙሪያ ምንምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ አስተዋጽኦ ንደፉ፡፡ ከዚያም በነደፋችሁት አስተዋጽኦ መሰረት የድርሰታችሁን ረቂቅ ጻፉ፡፡ ለጓደኞቻችሁ በማሳየት የማሻሻያ ሐሳብ ተቀበሉና ድርሰታችሁን እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

ለክፍል ከማቅረባችሁ በፊት ድርሰታችሁ ከሰዋስው፣ ከስርዓተ ነጥብ፣ ከሃሳብ ፍሰት፣ ወዘተ. አንጻር ያሉበትን ችግሮች እየተወያያችሁ ማስተካከላችሁን አረጋግጡ፡፡

2. በሚከተሉት ርዕሶች በቡድን ሁናችሁ አንድ አስረጅ ድርሰት ጻፉ፡፡ከጻፋችሁ በኋላ የሰዋስው ግድፈቶችን፣ የሃሳብ ፍሰትን፣ ወዘተ በማረም እንደገና በመጻፍለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

1. ‹‹የጊዜ አጠቃቀም›› በሚለው ርዕስ ቢጋር አዘጋጁ።

2. ባዘጋጃችሁት ቢጋር መሠረት ሦስት አንቀጽ ያለው አስረጅ ድርሰት ጻፉ።

ቦሰና(2013)በመጥቀስ ከተጠቀሙባቸው ውስጥ ለዚህ ጥናት እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ

ክፍል ሁለት

የአረጋውያን ሚና

<< መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን >>

<<ዕድሜ መስታወት ነው።>>ይህ አባባል ሰዎች እድሜያቸው እየገፍ ሲሄድ ከህይወት ያካበቱት ልምድና እውቀት ጥልቅና ሰፊ መሆኑን ለማመልከት የሚነገር ነው።

አረጋውያን ከህይወት ብዙ የተማሩ ፣በአያሌ የኑሮ ወጣ ውረዶች ተፈትነው ያለፉ የእድሜ ባለጸጎች ናቸው። ከህይወት ልምዳቸው ጥቂት በጨለፍን ቁጥርም ሚዛን የሚዳፋ ቁምነገር አናጣም።

አረጋዊየን በዕድሜ መግፍት የተነሳ አካላዊ ቅልጥፍናቸው እየደከመ ቢሄድም አንኳን አቅማቸው በፈቀደው መጠን በተለያዩ የስራ መስኮች ተሰማርተው ልናገኛቸው አንችላለን፤ይሁን እንጂ፣በዚህ አድሜያቸዉ በማህበረሰቡ ጎልቶ የሚታየው የጉልበት ተሳትፍቸው ሳይሆን አዕምሯዊ ሀብታቸው ነው። አረጋውያን ታዳሚዎችን ሰነ ምግባር በማስተማር ና በመምከር፣ በግለሰብ መካከል ይሁን በቡድን የሚፈጠሩ ግጭቶችን በማርገብና በመሸምገል በተለያዩ ግዜያት የተፈጠሩ ተፈጥሯዊ ና ሰው ሰራሽ ክስተቶችን ለአድሱ ትውልድ በመንገር ታሪክን የማስተላለፍ ና የመመስከር ከፍተኛ ሚና አላቸው።

(ከ2004 ዓ.ም ከአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ከገጽ92ላይየተወሰደ።)

1,ከላይ በቀረበው ጽሑፍ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ናሐራጋት ተመሳሳይ ፍች ስጡ ።

ሀ , የዕድሜ ባለፀጋ

ለ , ሚዛን የሚደፍ

ሐ , አፅምሯዊ ሀብት

መ, የስራ መስክ

ሠ ,መሽምገል

2, ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ቢጋር በማዘጋጀት አስረጅ ድርሰት ረቂቅ አዘጋጁ። ረቂቁን እንደገና በማንበብ የማስተካከያ ሀሳብ አቅርቡና እንደገና በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ ።

ሀ, የሀይል አጥረት

ለ,የአየር ንብረት መዛባት

ሐ, የአፈር መሸርሸር

ክፍል ሶስት

ቅርሶቻችን

ቅርስ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲተረጎም ፣ የህዝቦች ማንነትየሚገለጽበት ናየረጅም ዘመን ባህላቸውንና ታሪካቸውን እንዲገነዘቡ የሚረዳ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት ነው።ቅርስ።ከምንጩ አንጻር ባንድ በኩል በተፈጥሮ የታደልነውን ተፈጥሯዊ ቅርስ ሲመለከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካለፈው ትውልድ የወረስነውን ሰዎች የፈጠራ ስራን፣ባህላዊ እና ታሪካዊ ውጤቶችን የሚመለከት ነው።ሰው ሰራሽ፣ታሪካዊና ባህላዊ የሆነው ቅርስ ግዝፈት ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል።የሀገራችን የቅርስ ጥናት ናጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፩፻፱/፲፱፻፺፩የቅርስን ቁሳዊ ናመንፈሳዊ ይዘት ሲያብራራ <<ቅርስ ማለት በቅድመ ታሪክ እና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የሰራ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ፣የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚገልጽ ና የሚመሰክር በሳይንስ፣ በታሪክ፣ በባህል በሰነ ጥበብና በዕደ ጥበብ ይዘቱ ከፋተኛ ተፈላጊነት ናዋጋ ያለው ማንኛውም ግዙፍነት ያለውና የሌለው ነገር ነው >>ይለዋል።

ሰው ሰራሽ ፣ታሪካዊ ባህላዊ ቅርስ ግዝፈት ያለውና የሌለው ተብሎ ለመከፈል የራሱ መመዘኛዎች አሉት፡፡ ግዝፈት ያለው ቅርስ ቀደምት አባቶችና እናቶች መሰረታዊና እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሰርተውትና ተጠቅመውበት ትተውት ያለፉትን በዓይን ሊታይ በእጅ ሊዳሰስ የሚችለውን ሁሉ አጠቃሎ ይይዛል፡፡ በአንጻሩ ግዝፈት የሌለው ቅርስ፣ በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግት ነገር ግን፣ በዓይን ለመታየት ናበጆሮ ለመስማት የሚችል ሲሆን፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ልዩ ልዩ ትርኢቶች ና ጨዋታዎች፣ የጋብቻና የሀዘን ስነ ሥርዓቶች ና ተመሳሳይ የማህበረሰቡ ወግና ልማዶች ተጠቃለው የሚመደቡት ነው፡፡

(ጥር 26/2000 በቅርስ ምዝገባ ናቁጥጥር መምሪያ ለተካሔደ ሲምፖዚየም ከተዘገጀ ጽሑፍ ተሻሽሎ የቀረበ)

1, ከላይኛው በቀረበው ጽሑፍ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት እና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

ሀ, መንፈሳዊ ሀብት

ለ,የፈጠራ ስራ

ሐ, ግዝፈት

መ, ዕደ ጥበብ

ሠ,ወግ

2,ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መረጣችሁ አስረጅ ድርሰት ጻፍ፡፡ በመረጣችሁት ርዕስ ዙሪያ ምንምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ አስተዋጽኦ ንደፉ፡፡ከዚያም በነደፍችሁት አስተዋጽኦ መሰረት የድርሰታችሁን ረቂቅ ጻፍ ለጓደኞቻችሁ በማሳየት የማሻሻያ ሀሳብ ተቀበሉና የ ድርሰታችሁን ረቂቅ ጻፍ፡፡ለጓደኛቻችሁ በማሳየት የማሻሻያ ሀሳብ ተቀበሉና ድርሰታችሁን አንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ, የዱር እንስሳት መሰደድ

ለ, የህጻናት አንክብካቤ

ሐ, የድርቅ መከሰት

መ, ባህላዊ ጋብቻ

ክፍል አራት

<< የሰራ ያገኛል !>>

ኢትዮጵያ በርካታ ህጻናት ና ወጣቶች ያሉባት ሀገር ናት። እነዚህን ወጣቶች የሚያሳድጉ ወላጆች፣ አካባቢዎች፣ መምህርት ቤቶች፣ ፖሊሲ አውጪዎች ና ፖለቲከኞች ስራ ፈጣሪያችን የማብዛት ግዴታ አለባቸው። ልጆች ትልልቅ ርዕይና አላማ እንዲይዙ በቂችሎታና ሙያ እንዲኖራቸው ከሁሉም በላይ ወላጆች ሀላፊነት አለባቸው።በሁሉም መስፈርቶች እያደገ የሚሔድ የሚሄድ ቤተሰብ ሀላፊ የሆኑ ወላጆች የኗቸው ልጆች፣ ውስጣቸውን እየመረመሩ የቤተሰባቸውን እንቅስቃሴ ወደተሻለ ህይወት የሚቀይሩና ለልጆቻቸው ምሳሌ መሆን የሚችሉ ወላጆች የኗቸው ልጆች ከወላጆቻቸው የበለጠ ባለ ራዕይ ይሆናሉ። ህይወት የተለያዩ አማራጮች እንዳሏት ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ፣ በሂደት የነሱ ህይወት ከዕለት ወደ ዕለት ለውጥ አያመጣ ሲሄድ፣ በየቤተሰቡ ያለ አንድ ሁለት ሰው የራሴ የሚለው ስራ ሲፈጥር ተነሳሽነት ያድጋል፤<<ልምድ የካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸው ዩኒቨርስቲዎች ናቸው።

አሁን አሁን አነደሚታየው ወላጆች በጣም ውስን የሆነ ህልምና ራዕይ አላቸው። የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ሁሉ ከቤተሰብ አባላት ና ከልጆች መኖር አለመኖና ጋር የሚያያይዙ አሉ። በመሰረቱ ህጻናት ወላጆቻችን አስገድደው የተወለዱ አይደሉም፤ ህጻናትን የምንወልዳቸው እኛ ነን።ከምንጠቀምበት በላይ ገቢ ለመፍጠር የሚንቀሳቀስ ወላጆች ስንበዛ በየቤቱ ያለ ድህነት ቀስ በቀስ ይጠፍል።ኢትዮጵያ የምታድገው እያንዳንዱ ቤተሰብ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ነው።

የኢትዮጵያ ትልቁ ሀብት ወጣቱ ነው።ወጣቱ አስተሳሰቡ ብሩህ ነው፤ ትኩስ ጉልበት አለው፤ከፍተኛ የመፍጠር ችሎታ አለው፤ፈጣን ነው፤አንድ ግዜ የጀመረውን ነገር ደጋግሞ በመስራት ለማሸነፍ ሰፊ የዕድሜ ገጸ በረከት የለው የህብረተሰባችን ክፍል ነው። ከማንም የተሻለ መኖር የሚፈለገው ወጣቱ። ይህንን ሁሉ ለማድረግ ብዙ መስራት ያለበት ወጣቱ

ነው።በጥቂቶች የኢኮኖሚ ነጻ መዉጣት ብዙ ሰው ጥሩ ኑሮ መኖር አይችልም ።የአስተሳሰብ ድህነትን የሚያወርሱት ልጅ ባለጸጋ አይሆንም፤ አትሆንም። ስለዚህ ሰራ ፈጣሪ ለመሆን የበለጠ እድልላለው ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል የስራ ፍላጎትና ተነሳሽነትን እናስተምረው ።

(ወሮታው በዛብህ፣ ኢንተርፕሬነርሽፕ፣ 1998፣109 ለማስተማር አንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ።)

1, ከላይ በቀረበው ጽሑፍ መሰረት ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።

ሀ, የአስተሳሰብ ድህነት

ለ,ውስን ህልምና ራዕይ

ሐ, ለልጆች ምሳሌ መሆን

መ, የዕድሜ ገጸ በረከት ስሞን

ሠ, ልምድ የካበተ

2, የሰራ ያገኛል የሚለውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ ጽሁፍን መሰረት አድረጋችሁ አሰተዋጽኦ ንደፍ ።

3,ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ አስረጅ ድርሰት ፃፉ።በመረጣችሁት ርዕስ ዙርያ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ አሰተዋጽኦ ንደፉ።ከዚያም በነደፋችሁት።አስተዋጽኦ መሠረት የድርሰታችሁን ረቂቅ እንደገና አስተካክላችሁ ጻፍ።

ሀ,ወጣትነት

ለ,ትዝታ

ሐ,የዕጽዋቶች ጥቅም

መ, ታላላቆችን ማክበር